የኢትዮጵያ
ኢንተርፕራይዝ ልማት

# ዝክረ ማኑፋክቸሪንግ

ቅጽ 1 ቁ. 1 መጋቢት 2015



## የኢትዮጵያ አዲሱ የሽግግር ምዕራፍ መንሳፈፊያ መርከቡና መቅዘፊያው የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎች መስፋፋት ነው!

**ክቡር አቶ መላኩ አለበል**
**የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ሚኒስትር**

በኢትዮጵያ ኢንተርፕራይዝ ልማት በኮሙኒኬሽን ጉዳዮች የተዘጋጀ

# ማውጫ


1 የአዘጋጁ መልዕክት 1

2 የዋና ዳይሬክተሩ መልዕክት 2

3 ቆይታ 4

4 ከስኬት መንደር 11

5 ልማት 14

6 ፋሲሊቴሽን 18

7 አቅም 22

8 እንስቷ 27

9 መዝናኛ 30

10 ካሜራችን 32



በኮሙኒኬሽን ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት የተዘጋጀ

ዋና አዘጋጅ፦ አሸናፊ መለሰ

አዘጋጅ፦ ሮቤል አህመድ

ዮሃንስ ምሳው

ፀሃይነሽ መንግስት

ፎቶ ግራፍ፦ ያለም ፍሬ በቀለ

ስርጭት፦ ሃና ፋንቱ

# የአዘጋጁ መልዕክት

አምራችነት ጃፓንን የስልጣኔ ቁንጮ ያደረገ፣ ሲንጋፖርን ከተራ ወደብ ከተማነት ወደኢኮኖሚ ማዕከልነት የመነደገ፣ አሜሪካን ኃያል፣ ኢራንን ብርቱ፣ እስራኤልን ምጡቅ፣ ጀርመንን ተመራጭና ቻይናን የፈጣን ኢኮኖሚ ባለቤት ያደረገ ነው፡፡

አምራችነት እንዲሁ የሚታደሉት ሳይሆን የትውልዶችን ትንቅንቅ የሚፈልግ፣ በጥረትና በላብ የሚካኑት ማሕበረሠባዊ አስተሳሰብ፣ ሐገራዊ የዕድገት አቅም ነው፡፡

ኢትዮጵያም ያሏትን ተፈጥሯዊ ስጦታዎች እንደዋነኛ የዕድገት መሠረቷ በመያዝ፣ በውስን ካፒታል በርካታ የስራ ዕድልን መፍጠር የሚችሉ፣ በቀላል የአስተዳደር ወጪ በእግራቸው የሚቆሙና እንደገበያው ሁኔታ ራሳቸውን እየለዋወጡ በማያቋርጥ የስኬት ጎዳና ለመራመድ የሚያስችሉ የአምራች ኢንተርፕራይዞች ልማትን ከተዋወቀች ዋል አደር ብላለች፡፡
በእነዚህ ዓመታት በአስር ሺዎች የሚቆጠሩ  አምራች ኢንዱስትሪዎችን ለመፍጠር ተችሏል፡፡ በዚህም በመቶ ሺዎች የሚቆጠሩ ዜጎች ቋሚ የስራ ዕድል ማግኘት ሲችሉ ከፍተኛ የሆነ የቴክኖሎጂና የክህሎት ሽግግሮችም በመካሄድ ላይ ናቸው፡፡

በመሆኑም ይህንኑ አቅም ይበልጥ ለማጎልበት፣ በጠንካራ የአስተሳሰብ ቅኝት ላይ እንዲመሠረትና ልማቱ የሁሉም መሆን እንዲችል የተቋማችን የኮሙኒኬሽን ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት ዘርፉን ለማስተዋወቅና ስራዎችን በእውቀት ለመምራት የሚያስችሉ መረጃዎችን በማሠራጨት ውጤታማና ምቹ የዘርፍ ልማት እንዲኖር ጥረት በማድረግ ላይ ይገኛል፡፡
ይህ በተቋሙ ታሪክ የመጀመርያ የሆነው ዲጂታል መፅሔትም በዘርፉ እንደሐገር እየተከናወኑ የሚገኙ ጉዳዮችን ከማስተዋወቅም ባለፈ በተቋም ደረጃ የሚገኙ ባለሙያዎች ያዘጋጇቸውን ዕውቀት ተኮር መጣጥፎች በማካተት በአምራች ኢንተርፕራይዝ ልማቱ ዙርያ ለተሠባሰቡ ተደራሲያን አንዳች ቁም ነገር ለማስጨበጥ ጥረት ተደርጎበታል፡፡

ከሁሉ በላይ ደግሞ ከኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ሚኒስትር  ከክቡር አቶ መላኩ አለበል ጋር ባደረግነው ቆይታ በኢትዮጵያ ኢንተርፕራይዝ ልማትና በዘርፉ አዳዲስ ተለዕኮዎች ዙርያ የጠራ ዕይታን ለማስያዝ ጥረት አድርገናል፡፡

በመሆኑም በመፅሔቷ እየተዝናናችሁ ቁምነገር ትሸምቱ ዘንድ እየጋበዝን በመፅሔት ዝግጅትም ሆነ ማንኛውንም የህዝብ ግንኙት ስራችን ላይ አስተያየት ካላችሁ፣ እንዲሁም በዚሁ መጽሔት እንዲታተም የምትፈልጉት መጣጥፍም ካለ በአድራሻችን ብትልኩልን ለማስተናገድ በራችን ክፍት መሆኑን በዚህ አጋጣሚ እናሳውቃለን፡፡

**መልካም ንባብ !**

**አሸናፊ መለሠ**

**የኮሙኒኬሽን ጉዳዮች  ዳይሬክተር**

# የዋና ዳይሬክተሩ መልዕክት



ከበለፀጉ አገራት ልምድ እንደሚታየው የአምራች ኢንዱስትሪ ዘርፍ በአንድ ወቅት ርብርብ ብቻ የሚሳካ የኢኮኖሚ እድገት አማራጭ አይደለም። ሃገራዊ የተቀናጀ የፖሊሲ ትኩረትና እይታ የሚፈልግ፣ በሂደቱ ከሚገኘው ልምድና ትምህርት እያደገ የሚሄድ የተግባር ልምምድን የሚጠይቅ ነው።

አገራችን በአምራች ኢንዱስትሪ ዘርፉ ጠንካራ ኢኮኖሚን ለመገንባት እየተጓዝንባቸው ባሉ እንቅስቃሴዎች አበረታች ሊባሉ የሚችሉ ውጤቶችን እያስመዘገበች ትገኛለች። በየጊዜው የሚገኙ ልምዶችን መነሻ በማድረግም አስፈላጊ የፖሊሲና የተግባር ማስተካከያዎችን እያደረግን ይበልጥ የተሻሉ አፈፃፀሞችን ለማስመዝገብና ከዘርፉ ሊገኝ የሚችለውን ኢኮኖሚያዊ አቅም ለሀገራዊ እድገት ለማዋል ከፍተኛ ጥረት እያደረግን እንገኛለን።

የኢፌዲሪ መንግስት አምራች ዘርፉን የማስተባብርና ተዋናይ አካላትን በማቀናጀት በዘርፉ የተሰማሩ ኢንተርፕራይዞች እንዲስፋፉና እንዲጠናከሩ፣ አስፈላጊ መሰረተ ልማቶች እንዲለሙ እና ተጠቃሚ እንዲሆኑ የሚሰጠዉን ድጋፍ ለማስፈጸም እንዲቻል በአዲስ መልክ የኢትዮጵያ ኢንተርፕራይዝ ልማት አደረጃጀት፣ ስልጣንና ተግባር መወሰኛ ደንብ ቁጥር 526/2015 ፀድቆ ስራ ላይ እንዲዉል አደርጓል። ይህም ዘርፉ ላይ የሚታዩትን ተግዳሮቶች በመፍታት የኢንተርፕራይዞችን የማምረት አቅም በማጎልበት የዘርፉን ምርታማነት ለማሻሻል፣ ተኪ ምርቶችን በዓይነትና በብዛት ለማምረት፣ የኤክስፖርት ምርትን ለማስፋትና የሚፈጠረዉን የስራ ዕድል ለማሳደግ ትልቅ ጠቀሜታ ይኖረዋል።

ለዘርፉ ልማት የምንሰጠው ድጋፍ ኢንተርፕራይዞች ላይ በቀጥታ ውጤት ማምጣት እንዲችል በእውቀት ላይ የተመሰረተ እንዲሆን ማድረግ ያስፈልጋል። ለዚህ ደግሞ አስፈፃሚው አካል ብቃት ያለው ድጋፍ የማድረግ አቅሙ እንዲጎለብት ተቋሙ የአቅም ግንባታ ስልጠናዎችን ለክልሎችና ለባለድርሻ አካላት እየሰጠ ይገኛል። በቀጣይም ክፍተትን መሠረት ባደረገ አግባብ በስፋት የሚሰራበት ይሆናል።

እነዚህን ተግባራት ለማሳካት እንዲቻል የአነስተኛና መካለለኛ አምራች ኢንተርፕራይዞች ልማት የአስር ዓመታት ፍኖተ ካርታ /Road Map/ ዝግጅት እየተከናወነ ይገኛል። ይህም ዘርፉ አሁን ያለንበትን ነባራዊ ሁኔታና የሚስተዋሉ ችግሮችን በመዳሰስ፣ በሚቀጥሉት አስር ዓመታት ዘርፉ መድረስ የሚችልበትን ደረጃ ማመላከት፣ የሚከናወኑ ተግባራት አቅጣጫዎችና ለችግሮቹ የመፍትሔ አማራጮችን ማስቀመጥ የሚችል እንዲሆን ልዩ ልዩ ስራዎች በመሰራት ላይ ይገኛሉ።

ከዚህ በተጨማሪ ለአነስተኛና መካከለኛ አምራች ኢንተርፕራይዞች ልማት ውጤታማነት የሚረዱ የኤክስቴንሽን አገልግሎት፣ የፋይናንስ አቅርቦት እንዲሁም የማምረቻና መሸጫ ቦታዎች አቅርቦትና ልማት ስራዎችን የተመለከቱ ጥናቶችና የስትራቴጂ ዝግጅት መነሻዎች በመከናወን ላይ ሲሆኑ እነዚህ ጥናቶች ሲጠናቀቁ ከፍተኛ አስተዋፅኦ ያደርጋሉ ተብሎ ይጠበቃል።

የአነስተኛና መካለለኛ አምራች ኢንተርፕራይዞች ልማት ስራ የተለያዩ አካላትን ተሳትፎና ቅንጅት የሚጠይቅ በመሆኑ ለዘርፉ ስኬታማነት ሁሉም የድርሻውን እንዲወጣ በዚህ አጋጣሚ ጥሪዬን አቀርባለሁ።

**አመሠግናለሁ!**

**አለባቸው ንጉሤ /ፒ.ኤች.ዲ/**
**የኢትዮጵያ ኢንተርፕራይዝ ልማት**
**ዋና ዳይሬክተር**



# ቆይታ

## የኢትዮጵያ አዲሱ የሽግግር ምዕራፍ መንሳፈፊያ መርከቡና መቅዘፊያው የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎች መስፋፋት ነው!

ክቡር አቶ መላኩ አለበል
የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ሚኒስትር

ጤና ይስጥልን! የዚህ እትም ልዩ የመፅሔታችን እንግዳ የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ሚኒስትር ክቡር አቶ መላኩ አለበል ናቸው፡፡

ተቋማችን በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 526/2015 "የኢትዮጵያ ኢንተርፕራይዝ ልማት" በሚል መጠርያ በአዲስ መልክ መቋቋሙን ተከትሎ ተቋሙ ምን አዲስ ተልዕኮዎችን ታሳቢ እንዳደረገ፣ የቀጣይ ጊዜያት የትኩረት አቅጣጫዎቹ በምን ዙርያ እንደሚያተኩሩና ለኢንተርፕራይዝ ልማቱ ስላሉ እድሎች በተመለከተ ጥያቄዎችን አቅርበንላቸዋል፡፡

ክቡር ሚኒስትሩም እጅግ ጠቃሚ ቁምነገሮችን አካፍለውናል፡፡ እንድታነቡ ተጋብዛችኋል



### የኢንተርፕራይዝ ልማት ለኢትዮጵያ ምን ትርጉም አለው?

ኢንተርፕራይዝ ልማት ለኢትዮጵያ በርካታ ጥቅምና ትርጉም ያለው ነው፡፡ `በዓለም ላይ ዛሬ አደጉ የምንላቸው አገሮች ከየት ተነስተው፣ ምን አይነት የእድገት መሰላልን ተከትለው፣ ምን አይነት የእድገት መንገድን አልፈው ነው እዚህ የደረሱት?` ብንል ጥቃቅን ኢንዱስትሪዎችን አሳድገውና አስፋፍተው አነስተኛዎቹ ኢንዱስትሪዎች መካከለኛና ከፍተኛ ኢንዱስትሪዎችን ኢንዲፈጥሩ በማድረግ ነው፡፡

ምርምርና ጥናትን፣ ስራ ፈጠራንና አዳዲስ ሀሳብን በማፍለቅና የፈለቀውን ሀሳብ ወደ ተግባር ማስገባት በመቻላቸው ምክንያት በአለም ላይ የቴክኖሎጅ ልዩነት እንዲፈጠር ሆኗል፡፡ ይህም ቴክኖሎጅ ያለውና የሌለው፣ ቴክኖሎጅ የሚጠቀምና የማይጠቀም፣ በቴክኖሎጅ የሚያመርትና የማያመርት መካከል ልዩነት በመፈጠሩ ምክንያት አለም ላይ የአገራት እድገት ከፍና ዝቅ ብሎ ልናየው ችለናል፡፡

ስለዚህ ኢንተርፕራይዞችን በምናስብበት ጊዜ ከመነሻ ሀሳቡ የአንድ አገር ጥራት ያለው ኢኮኖሚ የሚገነባው፣ ዜጎች ገቢያቸው ሊሻሻል የሚችለው፣ ቀጣይነት ወዳለው ምርምርና የቴክኖሎጅ እድገት ውስጥ ሊገቡ የሚችሉት ከጥቃቅን ኢንዱስትሪዎች ጀምሮ እስከ ከፍተኛው ድረስ ማደግ የሚችሉበት ምቹ ሁኔታ ሲፈጠር ነው፡፡

ኢንተርፕራይዝ ልማት የስራ እድል የመፍጠር ብቻ ተደርጎ ሊታይ የሚችል አይደለም፡፡ ኢንተርፕራይዝ ልማት በአንድ አገር ላይ ፍትሐዊ የሆነ የሐብት ስርጭት እንዲኖር ለማድረግ ያስችላሉ፡፡ ለዚህም መሰረቱ ሰፊ የሆነ ጥቃቅን ኢንተርፕራይዞች መኖር መቻል አለባቸው፡፡

ዜጎች የተሻለ ሀብት የሚያመነጩበት፣ የተሻለ ምርት የሚያመርቱበት፣ ገቢ ምርትን የሚተኩበትና ኤክስፖርት ሊያደርጉ የሚችሉበትን እድል የሚፈጠሩባቸው በዚህ መንገድ ነው፡፡ ሰለዚህ ኢንተርፕራይዝ ልማት ስንል ሰፋ አድርገን ስናየው የኢትዮጵያን አጠቃላይ እድገትና የወደ ፊት እጣ ፈንታ፣ የዜጎችን የስራ እድል የማግኘት ሁኔታን፣ የኢትዮጵያን የገቢና የወጪ የንግድ ምጣኔ፣ የውጭ ምንዛሬ ግኝትን የሚያሳድግ ዘላቂነት ያለው የምርምር፣ የስርጸትና የእድገት ሁኔታን የሚወስን ክፍል ማለት ነው፡፡

ይህ ዘርፍ ቴክኒክና ሙያዎችን፣ ምርምርና ጥናትና ስልጠና የሚሰጥባቸውን ዩኒቨርስቲዎችን ዘርፉን ለማሳደግ ሚና ያላቸው መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማትን ሁሉ የሚያንቀሳቅስ ሠፊ ዘርፍ ነው፡፡ አንድ ኢንተርፕራይዝ በምልዓት ውጤታማ መሆን የሚችለው እነዚህ ሁሉ ባለድርሻዎች በሃላፊነትና በጥበብ ዘርፉን ማገዝ ሲችሉ ነው፡፡

በሌላ መንገድ የኢንተርፕራይዞች ውጤታማነት የአገር ውጤታማነትን ይወስናል፤ የኢንተርፕራይዞች ውጤታማትነት የዜጎችን ውጤታማነት ይወስናል፤ የኢንተርፕራይዞች ውጤታማነት የትምህርት ተቋማትን ውጤታማት ይወስናል፤ የትምህርት ተቋማት ውጤታማነት በሌላ በኩል ደግሞ የኢንተርፕራይዞችን ውጤታማነት በመወሰን ረገድ ሚና ይኖረዋል ማለት ነው፡፡

በመሆኑም ዘርፉ የመንግስትን በኢኮኖሚ ሽግግር ውስጥ ሊያሳካው የሚፈልገውን የማህበረሰብ ብልፅግና ራዕይ እውን ለማድረግ መሰረት የሚጣልበት ዘርፍ ነው ብሎ መውሰድ ይቻላል፡፡

## የኢንተርፕራይዝ ልማት ለኢትዮጵያ ምን ትርጉም አለው?

**ዋና ዋና ተልዕኮ አድርገን ልንወስደው የምንችለው፡ -**

አንደኛ፡- ወደዚህ ዘርፍ የሚገቡ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን ስራውን እንዲያውቁትና እንዲለምዱት ሁኔታዎችን በተገቢው ሁኔታ እንዲረዱ ግንዛቤ መፍጠር እንደ አንድ ተግባር ልናየው እንችላለን፤

**ሁለተኛው፡-** ወደ ዚህ ስራ ለሚገቡ ኢንተርፕራይዞች ምቹ ሁኔታን የመፍጠር ተልዕኮ ነው፤

**በሦስተኛነት፡-** ኢንተርፕራይዞች ወደ ስራ ከገቡ በኃላ የሚያስፈልጋቸው ድጋፎችን እንዲያገኙ የማድረግ ስራን መስራት ሲሆን፤

**አራተኛ፡-** እነዚህ ተቋማት በተለያዩ ድጋፎች ካልሆነ በስተቀር ብቻቸውን ውጤታማ መሆን ስለማይችሉ ድጋፉን የሚሠጡ ባለድርሻዎችን እንቅስቃሴ የማስተበበር ስራ አድርገን ልንወስድ እንችላለን፤

**አምስተኛው፡-** ኢንተርፕራይዞቹና ኢንተርፕረነሮቹ የሚፈለፈሉበትን ምቹ ሁኔታዎችን መፍጠር ነው፡፡ ይህ እጅግ በጣም አስፈላጊ ስራ በመሆኑ ኢንተርፕሩነሮችን የማሰልጠንና ለእነሱ የሚሆኑ ቴክኖሎጅዎችን ማቅረብና ማለማመድ ያስፈልጋል፡፡ ለዚህም በሁሉም አካባቢዎች የስራ መፍጠሪያ ኢንኩቤሽኖችን የማባዛት፣ የመፍጠርና ውጤታማ እንዲሆኑ የማድረግ ጉዳይ አንዱ ተልዕኮ አድርገን ልንወስደው እንችላለን፡፡

በሌላ በኩል በኢንተርፕራይዝ ልማት ውስጥ አንደ ትልቅ ተልዕኮ ተደርጓ ሊወሰድ የሚገባው የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን አገልግሎት ነው፡፡ በዚህም ተከታታይነት ያላቸው የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን አገልግሎት የሚፈልጉ ኢንዱስትሪዎችን በውጤታማነት መደገፍ ተገቢ ነው፡፡

ይህ የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን አገልግሎት አጠቃላይ የኢንተርፕራይዞችን ውጤታማነት የሚወስን ስራ ነው፡፡ ሌሎች የፋይናንስ አቅርቦት፣ የመስሪያ ቦታ አቅርቦትና የገበያ ትስስር የመሳሰሉት ለዚህ ተቋም የተሰጡ ተልዕኮዎችና ተግባራት ተደርጎ የሚወሰዱ ናቸው ማለት ነው፡፡

## በቀድሞው አደረጃጀት ይታዩ የነበሩ ዋና ዋና ችግሮች የትኞቹ ናቸው? ችግሮቹን ለመሻገርስ በአዲሱ አደረጃጀት ምን የታሠበ ነገር አለ?

ቀደም ሲል በነበረው አደረጃጀት ከነበሩ ችግሮች መካከል አንደኛ ከፌዴራል እስከ ታችኛው መዋቅር ድረስ ያለመናበብ ችግር ነበር፡፡ አሁን ላይ ሙሉ በሙሉ ተፈቷል ባይባልም እሰከ ታች ድረስ ይህንን ለማሻሻል የተደረጉ ጥረቶች አሉ፡፡ እንደዚህ መሰራቱ ኢንተርፕራይዞችን ለመደገፍ የተሻለ አስተዋጽኦ ያበረክታል፡፡

ሁለተኛው የተቋማት ቅንጅታዊ አሰራር ችግር ነበር፡፡ አሁን የበለጠ ተቀራራቢነት ያላቸው ስራዎች ወደ አንድ እየተሰባሰቡ የሚሰሩበትን ሁኔታ እየተፈጠረ ነው፡፡ በተለይ ደግሞ ከዚህ ቀደም እንደ ኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን አይነት ወደ ሌሎች ተቋማት ሄደው የነበሩትን ስራዎች ወደዚህ ማምጣት መቻሉ የተሟላ ድጋፍ ለማድረግ የሚያስችል ሁኔታን ይፈጥራል፡፡

**ዓለም በኢንዱስትሪው አራተኛው ትውልድ (4th generation) ላይ ደርሷል፡፡ የእኛ ደግሞ ገና ጅምር ላይ ያለና ብዙ ክፍተቶች ያሉበት ስለሆነም ክፍተቶችን ለመሙላት የሚያስችሉ ስራዎችን ሌት ተቀን መስራት ይጠበቅብናል፡፡**



ከዛ ባለፈ የባንክና መሬት ላይ የነበሩትን ጉድለቶች ለማስተካከል የሚያስችሉ አሰራሮችን ጭምር በዚህኛው ማሻሻያ የተካተተ ስለሆነ ከዚህ በፊት ከነበረው ሁኔታ አንጻር የተሻለ ውጤት ሊያመጣ የሚችል ነው።

ነገር ግን ተጨማሪ የአሰራር ማሻሻያ፣ የአቅም ግንባታ ስራዎች፣ የአመራርና የባለሙያ ፈጠራ ስራዎች፣ የድጋፍ ማዕቀፎችና ስትራቴጅዎች ያስፈልጋሉ። እነዚህን አሟልተን ካልሆነ በስተቀር አደረጃጀት ብቻውን ብዙ ርቀት ሊወስደን አይችልም።

**በአዲሱ "የኢትዮጵያ ኢንተርፕራይዝ ልማት" ድጋፍ የሚደረግላቸው ኢንተርፕራይዞች በስርጭትም፣ በቁጥርም ከፍ ያሉ እንደሚሆኑ ይጠበቃል። ከዚሁ ጋር ተያይዞ የኢንተርፕራይዞች የድጋፍ ፍላጎቶችም ይጨምራሉ። ለዚህንና መሰል የድጋፍ ጥያቄዎች ምን ያክል ዝግጁነት አለ?**

ታዳጊ አገራት ላይ ያለው የእድገት ልዩነት እንደተጠበቀ ሆኖ እንደ ኢትዮጵያ ባሉ ታዳጊ አገራት የስራ አጥነት ችግር እጅግ በጣም ከፍተኛ ነው።

ስራ አጥነት ችግር አለ ማለት ዜጎች አያመርቱም ማለት ነው። ዜጎች ከማያመርቱባቸው ምክንያቶች መካከል አንዱ በእጃቸው የማምረቻ መሳሪያ የለም ማለት ነው።

ያን የማምረቻ መሳሪያ ችግር ከፈታንላቸው ዜጎች ከራሳቸው አልፈው ለሌሎች የስራ እድል የሚፈጥሩበት ሁኔታ ይኖራል።

እንደ ኢትዮጵያ በጣም ሰፊ የሆነ አምራች ሀይል አለ፤ ነገር ግን ለዚህ አቅም የሚሆን ምቹ ሁኔታ ባለመፍጠራችን ምክንያት አምራቹ ሀይል ስራ እየፈለገ ይገኛል።

የማምረቻ መሳሪያዎችን የማቅረብ ጉዳይ እንደ መንግስት የሞት ሽረት አጀንዳ መሆኑ አይቀርም። ይሄን ካላደረግን በስተቀር የመንግስትን መዋቅር በመለጠጥና የመንግስትን ቤት በማስፋት የስራ አጥነትን ችግር መፍታት አይቻልም።

ምናልባትም ያመረተውን ሳያስተርፍ የሚበላ የመንግስት መዋቅር እየተፈጠረ፣ ካፒታል ፕሮጀክቶች እየቀነሱ ህዝቡ ከመንግስት ላይ የሚጠብቀውን ልማት የሚያገኝበትን እድል እያሳጣ ነው የሚሄደው። ስለዚህ ጥቃቅን በምንልበት ጊዜ በዋናነት የመንግስትን ጫና የሚቀንስ ማለት ነው።

መንግስትን የስራ ዕድል እንዲፈጥርለት የሚጠይቀውን ዜጋ ቁጥር አቅጣጫውን አስቀይሮ ወደ ትክክለኛ መስመር እንዲገባ ያደርገዋል። በመሆኑም የግል ሴክተሮችና የመንግስት ተቋማት ይሄንን ችግር በመፍታት ረገድ ቀጣይ የርብርብ አቅጣጫችን ነው የሚሆነው።

ፍትሐዊ የሐብት ስርጭት እንዲኖር ማድረግ የሚቻለው እያንዳንዱ ዜጋ የማምረቻ መሳሪያ ኖሮት በእውቀት፣ በአቅሙና በካፒታሉ ልክ አምርቶ ወደ ገበያ የሚያስገባው ምርት እንዲኖር ማድረግ ስንችል ነው፡፡

ከዚህ አኳያ ስራው ሰፊና ከባድ ነው፡፡ ብዙ ተቋማትን በአንድ ላይ አምጥቶ ማስተባበርና ማሰራት ይጠይቃል፡፡ ነገር ግን ይህንን ካላደረግን በስተቀር ዘላቂነት ያለው የኢኮኖሚ እድገት ማምጣት ስለማይቻል እንደሚኒስትር መስሪያ ቤት በየደረጃው ያሉትን ኢንዱስትሪዎችን የመደገፍ ኃላፊነት የተጣለባቸውን የክልል መዋቅርንም ጭምር በመደገፍና በማስተባበር ይሄ ስራ ስኬታማ እንዲሆን የበኩላችን ሚና የምንወጣ ይሆናል፡፡

ይህን ካላደረግን የስራ እድል አንፈጥርም፤ አነስተኛ ኢንዱስትሪ የለንም፤ መካከለኛ ኢንዱስትሪም አይኖረንም፡፡ ስለዚህ የድህነት አዙሪት ውስጥ መውጣት የምንችልበት እድል አይኖርም፡፡ ከድህነት አዙሪት ለመውጣት የግድ በዚህ አካባቢ ያሉትን መሰናክሎችና ማነቆዎችን መፍታት የግድ ይላል ማለት ነው፡፡

የኢንዱስትሪ ልማት በስራው ክብደት ሳይሆን ስራው በሚያመጣው ውጤት ነው መታየት ያለበት፡፡

ከዚህ አንጻር ሚኒስቴር መስሪያ ቤታችንን ድጋፍ የማድረግ አቅም በማጠናከር የአሰራር ስርአቶችን በመዘርጋት አዳዲስ፣ ዲጅታል፣ ዘመናዊ አሰራሮችን ተግባራዊ የማድረግ ተግባራት የምናከናውን ይሆናል፡፡

በተጨማሪም የማህበረሰቡን ግንዛቤ የማዳበር፣ የአመራሩን አመለካከት የመቀየር፣ የመስሪያና የመሸጫ ቦታዎች እንዲዘጋጁ በማድረግ ስራዎችን በልዩ ትኩረት በመስራት እንደመንግስት ለህዝቡ የገባነውን ቃል ተግባራዊ በማድረግ ረገድ ሚኒስትር መስሪያቤቱ የበኩሉን ድርሻ ይወጣል፡፡

## የመፈጸምና ማስፈጸም አቅምን ለማሳደግና ተቋማዊ አቅምን ለመገንባት እንደ ሚኒስቴር መስሪያ ቤት ምን የታሰበ ነገር አለ?

አንዱ በሚኒስትር መስሪያ ቤታችን የትኩረት መስክ ተደርጎ የተወሰደውና በአስር አመቱ እቅድ ላይም በጉልህ የተቀመጠው የመፈጸምና የማስፈጸም አቅምን መገንባት ነው፡፡

ይሄ የአቅም ግንባታ ብዙ አይነት ባህሪዎች ያሉት ነው፡፡

ይሄ ካልተደረገ በስተቀር ከዚህ በፊት ከነበረው ችግር ልንወጣ አንችልም፡፡

**የሀገርን ፖለቲካ እንዳይረጋጋ ከሚያደርጉ ነገሮች መካከል አንዱ የኢኮኖሚ ችግር ነው፡፡ ይህንን መፍታት የሚቻለው ደግሞ ድሮ ስናመርት ከነበርንበት ስልት ወጥተን አዳዲስ የማምረቻ መሳሪያ፣ አዳዲስ የገበያ መዳረሻ አዳዲስ ወደ ቢዝነሱ የሚገቡ ሰዎችን ስንጨምር ነው፡፡ ለዚህ ደግሞ ትልቁ እድል ያለው ኢንተረፕራይዞች ልማት ላይ ነው፡፡**

ዋናው የስራችን ማጠንጠኛ ቁልፍ ተግባር ተደርጎ የሚወሰደው የመፈጸምና ማስፈጸም አቅም ችግሮችን መፍታት የአቅም ግንባታ ስራ መስራት ነው፡፡

ይህንን ስናደርግ በተሟላ ሁኔታ ውጤታማ የሆኑ ኢንተርፕራይዞችን፣ የመንግስት አስፈጻሚዎችንና የኢኮኖሚ ሽግግሮችን ማምጣት እንችላለን፡፡

ይሄ ተግባራዊ የሚሆንበት ራሱን የቻለ ሰነድም እየተዘጋጀ ነው፡፡

## ገበያ ለኢንተርፕራይዞች ምን ትርጉም አለው? ኤግዚቢሽንና ባዛር ማዘጋጀቱስ ምን ፋይዳ ይኖረዋል?

አምራችና ገበያ የአንድ ሳንቲም ሁለት ገጽታዎች ናቸው፤ ሊነጣጠሉ የሚችሉ አይደሉም፡፡ አምራች ኢንተርፕራይዝ ምርት የሚያመርተው ለምርቱ መዳረሻ የሚሆነውን ታላሚ ተጠቃሚ አስቦ ነው፡፡ ለምሳሌ በቀን አንድ ሺህ ልብስ የሚያመርት ኢንተርፕራይዝ የሚያመርተው ለራሱ ፍጆታ ሊሆን አይችልም፡፡ ስለዚህ ገበያ ከሌለ አምራች የለም ማለት ነው፡፡

ብዙ ጊዜ ገበያ ወይም ንግድ ለኢንተርፕራይዝ የደም ስር ነው የሚባለው ጥሬ ዕቃን፣ ጉልበትን፣ ምርትን፣ ገንዘብን ማንቀሳቀስ ካልተቻለ እድገት መምጣት ስለማይችል ነው፡፡

ስለሆነም የገበያ እድሎችን መፍጠርና ተጠቃሚው ምርቶቹን እንዲያውቅ ምቹ ሁኔታዎችን መፍጠር የአምራቾችን የማምረት አቅም ፍላጎትና ውጤታማነት የሚያሳድግ ነው፡፡

የጥሬ ዕቃ ግብዓት፣ የማምረት አቅም፣ የማምረቻ መሳሪያና ካፒታል ቢኖርም እንኳን የሚመረተው ምርት ገበያ ካላገኘ ኢንዱስትሪው ውጤታማ ሊሆን አይችልም። ስለዚህ ገበያ ለአምራች ኢንተርፕራይዞች በጣም ወሳኝ ነው።

ገበያ ውስጥ መሸጫና መግዣ ብቻ ሳይሆን ውድድርም አለ። የዋጋ፣ የጥራት፣ የቴክኖሎጂ ውድድር አብሮ ይዞ የሚመጣ ከመሆኑም በተጨማሪ የተጠቃሚዎችን ጠቃሚ አስተያየት ይዞ የሚመጣ ነው።

ስለዚህ የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪው ገበያ ላይ ትኩረት ተደርጎ መሰራት አለበት የሚባለውም ገበያ ውስጥ የሚፈጠሩ ውድድሮች የሚፈጥሩት ተጽዕኖ ሰፊ በመሆኑ ነው።

በሀገራችን ገና ፍላጎትን አልፈጠርንም። አንድ አርሶ አደር አብዛኛውን ጊዜ ፍጆታውን እራሱ በሚያመርተው ነው እየሸፈነ ያለው።

አንድ መቀየሪያ ልብስ ያለው አርሶ አደር ሁለትና ከዚያ በላይ እንዲኖረው ካደረግን፣ ጫማ ያልነበረው እንዲኖረው ከአንድ አልፎ ሶስትና አራት ጫማ እንዲኖረው ማድረግ ከቻልን ገበያ እየፈጠርን እንሄዳለን ማለት ነው።

እንዲህ አይነቱ ፍላጎት ከተፈጠረ ደግሞ 85 በመቶ ለሚሆነው አርሶ አደር ገበያ እየፈጠርን የምንሄድበት ሁኔታ ይፈጠራል።

ስለዚህ የ110 ሚሊዮን ህዝብ ገበያ፣ ሲሰፋም፣ በርከት ያሉ ምስራቅ አፍሪካ ላይ ያሉትን ህዝቦች ድምር የያዘ ገበያ ነው በዙርያችን ያለው።

ይሄው ገበያ ታድያ በአንድ ፖሊሲ፣ በአንድ አይነት መሰረተ ልማት፣ በጣም ተቀራራቢ በሆነ ባህልና ቦታ ላይ የሚፈፀም ግብይት በመሆኑ ለአምራቾቹ ሰፊ እድል ተደርጎ ሊወሰድ የሚችል ነው። ከዚህ አኳያ ገበያ ለአምራች ኢንዱስትሪ በጣም ትልቅ ሚና ያለው ነው።

አሁን ላይ ብዙ ምርት ከውጪ ይመጣል። ይህን ምርት በሀገር ውስጥ ማምረት መቻል አለብን። ምክንያቱም አንዱ የንግድ ሚዛናችንን እንዲዛባ ካደረገው ነገር መካከል በተመሳሳይ ወይም በተሻለ ዋጋ እንዲሁም የጥራት ደረጃ ላይ ያለ ምርት ቢኖርም ከውጭ ካልመጣ በስተቀር እርካታ አይሰማንም። ይህም ከግንዛቤና ከአመለካከት ጋር የሚመጣ ችግር ነው።

የቆዳ፣ የጨርቃጨርቅ፣ የአግሮ ፕሮሰሲንግ፣ የኬሚካል፣ የስፔር ፓርት የሚያመርቱ ኢንዱስትሪዎች አሉን።

**ለሀገራችን እድገት የምንጓጓ ከሆንን ለሀገራችን ምርቶች ቅድሚያ የሚሰጥ ገበያ፣ የዳበረ ገበያ፣ እየተሻሻለና እያደገ በጥራትና በዋጋ ተወዳዳሪ እየሆነ የሚሄድ ገበያ መኖር መቻል አለበት። ይህን ለማድረግም በየደረጃው የሚዘጋጁ ኤግዚቢሽንና ባዛሮች መሸጫ ብቻ ሳይሆኑ ልምድ መለዋወጫ፣ አስተያየት መውሰጃ፣ ነገ ከነገወዲያ አዳዲስ የመወዳደሪያ ስልት የሚፈጠርባቸው እንዲሆኑ ማስቻል ይገባል።**

**ከዚህ አኳያ** አምራች ኢንዱስትሪዎችን ከምንደግፍባቸው ስልቶች መካከል አንዱ ለእነሱ የሚሆን ገበያ መፍጠርና ገበያው ላይ ገዥ ብቻ ሳይሆን የምርት ጥራትን የሚያሳድጉ፣ ተወዳዳሪና አወዳዳሪ ሀሳቦችም ጭምር የሚገኙበት እንዲሆኑ የማስቻል ስራ ነው። በመሆኑ ይህን ድርብ ድርብርብ ተልዕኮ ለመፈፀም ኤግዚቢሽንና ባዛሮች ከፍተኛ ሚና አላቸው።

ስለሆነም ኤግዚቢሽንና ባዛሮችን በሀገር አቀፍ ብቻ ሳይሆን በክልሎች፣ በከተሞችና በየአካባቢዎች እየተስፋፉ መሄድ አለባቸው።

ምርት አካባቢን እያጠገበ ተደራሽነቱን እያሰፋ ሲሄድ ነው ወደ ዓለም የሚደርሠው።

እንደዚህ ያሉ ገበያዎችና ለኢንተርፕራይዞች የገበያ ትስስር የሚፈጥሩ ሁነቶች ተጠናክረው መቀጠል አለባቸው።

ለዚህ ደግሞ ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ አስፈላጊውን ድጋፍ ያደርጋል።

**በመጨረሻም ለዘርፉ አስፈጻሚዎች፣ ኢንተርፕራይዞችና ለህብረተሰቡ የሚያስተላልፉት መልዕክት ካለ?**

ኢትዮጵያ አሁን ላይ በመጠኑ፣ በአይነቱ፣ በባህሪው ለየት ባለ የሽግግር ምዕራፍ ላይ ትገኛለች።

የዚህ የሽግግር ምዕራፍ መንሳፈፊያ መርከቡና መቅዘፊያው የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎች መስፋፋት ነው። የሀገርን ፖለቲካ እንዳይረጋጋ ከሚያደርጉ ነገሮች መካከል አንዱ የኢኮኖሚ ችግር ነው።

ይህንን መፍታት የሚቻለው ደግሞ ድሮ ስናመርት ከነበርንበት ስልት ወጥተን አዳዲስ የማምረቻ መሳሪያ፣ አዳዲስ የገበያ መዳረሻ አዳዲስ ወደ ቢዝነሱ የሚገቡ ሰዎችን ስንጨምር ነው።

ለዚህ ደግሞ ትልቁ እድል ያለው ኢንተረፕራይዞች ልማት ላይ ነው።

ከዚህ አኳያ በየደረጃው ያለው ኢንተርፕራዞችን ለመደገፍ የተሰማራው አካል አዳዲስ ሀሳቦችን በመቀበል፣ በማምጣትና በመተግበር **ኢንተርፕራይዞችን በልዩ ሁኔታ በመደገፍ የኢትዮጵያ የወደፊት እድል ዕጣ እንዲቃና በማድረግ ረገድ ባለሙያዎችና አመራሮች ትልቅ ኃላፊነት አለባቸው።**

**ይህንን ሀላፊነት በተሻለ ሁኔታ መወጣት ከቻልን ሀገርን በፅኑ መሰረት መገንባት እንችላለን። ይህን ስናደርግ በስንዴ አንደለልም፤ ስንዴ መደራደሪያ ሆኖ አይቀርብም! ብድርና እርዳታ የምንሰጥ እንጂ የምንቀበል አንሆንም! የኛ አይንና ጆሮ የሚያየውና የሚሰማው አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችንና የገበያ መዳረሻዎችን እንጂ አዳዲስ የሚዘረጉ የእርዳታ እጆችን አይሆንም** ማለት ነው። ስለዚህ ህዝባችን በድህነት ውስጥ እንዳይኖር ከተፈለገ በኢንተርፕራይዞች ልማት ላይ ያለንን ኃላፊነት በተሟላ መንገድ መወጣት አለብን።

ትንንሾቹን ሳንንቅ፣ ትልልቆቹንም እንደጨረሱ ሳንቆጥር አሁንም ሰፊ አድማስ መኖሩን አውቀን መስራት ይኖርብናል።

ዓለም በኢንዱስትሪው አራተኛው ትውልድ (4th generation) ላይ ደርሷል።

የእኛ ደግሞ ገና ጅምር ላይ ያለና ብዙ ክፍተቶች ያሉበት ስለሆነም ክፍተቶችን ለመሙላት የሚያስችሉ ስራዎችን ሌት ተቀን መስራት ይጠበቅብናል።



የማኑፋክቸሪንግ ስራው አድካሚ ነው፤ ይሁን እንጂ ሁሉም ኢትዮጵያዊ ሀገር በተወረረችበት ጊዜ እንደ አንድ አሳቢ እንደ አንድ ተናጋሪ ሆነው በዓላማቸው ፀንተው ሀገርን ከመበታተን ለማዳን እንደዘመቱ ሁሉ ሁለተኛ ጠላታችን የሆነውን ድህነታችንንም ለመታገል መንቀሳቀስ ያስፈልጋል።

በስከዛሬው እንቅስቃሴ ተስፋ ሠጪ ውጤቶችን አይተናል፤ ይህንን ይበልጥ በአዲስ አሰራርና ፖሊሲ በማደስ የአምራች ኢንዱስትሪው ወደተሻለ ደረጃ እንዲሸጋገር ማድረግ ይኖርብናል። በዚህም የሀገራችንን ኢኮኖሚ ማሳደግ የሚቻለን ይሆናል።

የተቋሙን 80ኛ ዓመታችንን ስናከብርም ከዚህ በፊት በ80 ዓመታት የተሰራውን ስራ በ8 ዓመትና ከዚያ በታች ለማሳካትና ለማከናወን አቅደን መስራት ይኖርብናል።

ይህንን ማድረግ ከቻልን ኢትዮጵያን ማሻገር እንችላለን። ይህን እውን ማድረግ ከቻልንም ትውልድ ሲዘክረን ይኖራል።

# የማይዝሉ ክንዶች

በዮሐንስ ምሳው

አላማችንን፣ ሃሳባችንንና እቅዳችንን በተጨባጭ እውን የምናደርገው በስራ ነው። አእምሯችን ውስጥ የነበረውን ሃሳብ በውጨዊው ዓለም ላይ አካላዊ ይዘትና ቅርጽ እንሰጠዋለን፤ እሴትም እንፈጥርለታለን። እሴትን የሚፈጥረው ውጤታማ ስራ ነው። ህልውናችን የሚለመልመውና ብሩህ መንፈስ የምንጎናጸፍው እሴትና ጥረትን ባስተሳሰረ ውጤታማ ስራ ነው። በዘፈቀደ ሳይሆን፤ በህይወት ዓላማ ላይ የተመሰረተ በውስጣዊ ፍቅር የተሞላና በእቅድ የሚከናወን ውጤታማ ስራ ሊኖር ይገባል።

ያለጥረት ወይም ያለስራ የሚገኝ እሴት ወይም ውጤት የለም። የእሴትና የውጤት ዋጋ የሚመዘነው፤ በጥረቱና በስራው ነው። ስለዚህ በእንቅፋቶችና በጊዜያዊ ስሜቶች ወደ ኋላ ሳንል በአይበገሬነት ለእሴት ፈጠራ የሚያስፈልገውን ጥረት ሁሉ ለማከናወን በብርታት መስራት ያስፈልጋል።

እሴት የማይፈጥር ወይም ውጤት የሌለው ጥረት፤ ከንቱ ልፋት እንጅ ስራ አይደለም። አብዛኛዎቹ ሰዎች ስኬታማ የሚሆኑት የሚወዱትን ስራ እየሰሩ ሳይሆን የሚሰሩትን ስራ ስለሚወዱ ነው።

ይህ ሲሆን ደግሞ እራስን በማሻሻል አገርን መለወጥ እንደሚቻል የብዙ ሰዎች ተሞክሮ ምስክር ነው። የእያንዳንዳችን መልካም ስራዎች ራሳችን፣ ቤተሰቦቻችን፣ ማህበረሰባችንና አገራችን የመለወጥ አቅሙ ሰፊ ነው።

መንግስት ለኢንዱስትሪው መስፋፋትና ለአገራችን ኢኮኖሚ እድገትና ለአገር በቀል እውቀቶች ወንዝ ተሻጋሪ እንዲሆኑ የበኩሉን ሚና እየተወጣ ይገኛል። ዘርፉን የተሻለ ለማድረግ በፖሊሲና በመዋቅር በማደራጀት በርካታ ስራዎች እየተሰሩ ናቸው። ከአገራችን ተጨባጭ ሁኔታ አንጻር ችግር ፈች የሆኑ የፈጠራ ውጤቶችና ተተኪ ምርቶች አሁን ላይ አገራችን እጅጉን ትፈልጋለች። ለዚህ ደግሞ ወጣቶች፣ ምሁራንና ባለሐብቶች ድርሻቸው ከፍ ያለ ነው።

እኛም በዚህ መጽሔት ስኬት በሚለው አምዳችን በሲዳማ ክልል በሐዋሳ ከተማ ነዋሪ የሆነው፤ በተኪ ምርቶችና በፈጠራ ስራ የተሰማራ አንድ ወጣት ይዘንላችሁ ቀርበናል እንድታነቡት ከወዲሁ ጋበዝናቹህ።



ወጣት ጋሻው ኤዳኦ በሲዳማ ክልል የሐዋሳ ከተማ ነዋሪ ነው። ተወልዶ ያደገው የአገራችን ርዕሰ መዲና በሆነችው አዲስ አበባ ከተማ ነው።

"ከልጅነቴ ጀምሮ ብረት ከብረት በማጋጨት ሐሴትን፤ በማጣመም የተለያዩ ቅርጾችን በማስያዝ እንደ መጫዎቻነት እጠቀምበት ነበር" የሚለው ወጣት ጋሻው ከልጅነቱ ይዞት የመጣውን ፍላጎት ለማሳካት የአስራ ሁለተኛ ክፍል ትምህርቱን እንዳጠናቀቀ ሌሎች አማራጮችን ሳያይ መክሊቴ ነው ባለው ሙያ ለመሰማራት የሚያግዘውን የመጀመሪያውን የሙያ ትምህርት በአዲስ አበባ ሰላም የቴክኒክና ሙያ ማሰልጠኛ ኮሌጅ በጀነራል መካኒካል በዲፕሎማ ተመረቀ።

"የልጅነት ፍላጎቴን በእውቀትና በክህሎት በደንብ አዳብሬው ስለነበር ከተመረቅኩ በኋላ ለመቀጠር ጊዜ አልፈጀብኝም" የሚለው ወጣቱ በተለያዩ ተቋማት በተለያዩ ሙያዎች ለስምንት አመታት ሰርቷል።

በነዚህ አመታት የሰራቸው ስራዎችና ያገኘው ልምድ የራሱ የሚለውን ነገር ለመክፈት ሰፊ ተሞክሮ ያገኘበት ነበር። ይህንን እውን ለማድረግ ሰፊ ጥረት አድረጓል። ነገር ግን በወቅቱ የነበረው አማራጭ መደራጀት ነበር።

"ተቀጥሮ መስራት የሌሎችን ሐሳብ ተግባራዊ ለማድረግ ካልሆነ በስተቀር የኔነው የምለውን ሐሳብ ለመተግበር ምቹ ሁኔታ አልፈጠረልኝም፤ የራሴን ሀሳብ ለመተግበር እንደኔ ለመስራት የሚፈልጉ ወጣቶች ፈልጊ መደራጀት እንዳለብኝ ውስጤን በማሳመን እኔን ጨምሮ አምስት ወጣቶችን በማደራጀት እያንዳንዳቸው አምስት ሺህ ብር (5,000) በማዋጣት በሀያ አምስት ሺህ ብር (25,000) መነሻ ካፒታል በ 2007 ዓ.ም **ኤልሻሎም ኤሌክትሮ መካኒካል ኢንተርፕራይዝ** በሚል ስያሜ ማህበሩ ተመሰረተ።"

ካለው የስራ ተነሳሽነት ለሙያው ካለው ፍቅር አንጻር ወጣት ጋሻው የማህበሩ ሊቀመንበር በመሆን ተሾመ። የስራቸውን የመጀመሪያ ምእራፍ ለስራው በማይመች መልኩ በኪራይ ቤት ለአንድ አመት የተለያዩ ትንንሽ ስራዎች በመስራት እንደቆዩና በዚህ አንድ ዓመት ውስጥ በርካታ ችግሮች ቢገጥሟቸውም በወቅቱ ከብዷቸው የነበረው የሚሰሩት ስራና የሚከፍሉት የቤት ኪራይ ባለመመጣጠኑ ማኅበሩ ገና በለጋነቱ ፈተና ውስጥ እንደገባ ይናገራል።

ይህንንም ችግር ለመፍታት በአካባቢው የሚገኘውን የመንግስት አካል ስራቸውን እንዲያደዩላቸውና የገጠማቸውን ችግር እንዲፈቱላቸው ጠይቀዋል።

መንግስትም የሚሰሩትን ስራ በመመልከት ያለባቸውን ችግር በውል በመረዳት የመስሪያ ቦታ የሚሆን ሁለት መቶ (200) ካሬ ሜትር ቦታ እንደተሰጣቸው የሚናገረው ወጣት ጋሻው የተሰጣቸው ቦታ "ለችግራችን መፍትሄ ከመሆኑም በተጨማሪ ሌሎች የፈጠራ ስራዎችን እንድንሰራ በር ከፍቶልናል" ይላል።

ከሰሯቸው የፈጠራ ስራዎች መካከል የቆጮ መፋቂያና መጨመቂያ ማሽን ከሐዋሳ ዩኒቨርስቲ ጋር በመቀናጀት ጊዜና ጉልበትን የሚቆጥብና በብዛት ማምረት የሚችል ማሽን መስራት ችለዋል።

ለመስራት ያነሳሳቸው የአካባቢው ማህበረሰብ በአብዛኛው ቆጮ ለማምረት ከፍተኛ የሆነ ጉልበት እንደሚያውጡና የሚያመርቱት ምርት ከልፋታቸው አንጻር ሲታይ ዝቅተኛ መሆኑን ከመገንዘብ እንደሆነ ይናገራል።

አሁን ላይ ለሙከራ ሁለት ማሽኖችን በሲዳማ ክልል በቦንሳ ወረዳ እንደላኩና የማሽኑ ሁኔታ ታይቶ የሚስተካከለው ከተስተካከለ በኋላ በስፋት በማምረት በዝቅተኛ ዋጋ ለማህበረሰቡ ተደራሽ በማድረግ የመፍትሄ አካል ለመሆን በትጋት እየሰሩ ነው።

በኤልሻሎም ኤሌክትሮ መካኒካል ኢንተርፕራይዝ ማህበር የዳቦ መጋገሪያ፣ የሊጥ ማቡኪያ፣ የቡና መፍጫና መቁያ፣ የመኖ ማቀነባበሪያ፣ የፈሳሽ ሳሙና ማምረቻ፣ የቡሎኬት ማምረቻና የስሚንቶና የአሸዋ መቀላቀያ (ሚክሰር) ማሽኖች እያመረቱና ጥገና እየሰጡ እንደሆነ ወጣቱ አጫውቶናል።

የማህበሩ ሊቀ መንበር ተተኪ ምርቶች በአገር ውስጥ ኢንተርፕራይዝ መመረታቸው በርካታ ጥቅሞች እንዳሉዋቸውና በዋናነት የውጪ ምንዛሬ ማስቀረት እንደሚቻል፣ ከውጭ ከሚመጣው ማሽን አንጻር ዋጋው ቅናሽ መሆኑ፣ ለዜጎች በስፋት የስራ ዕድል መፍጠሩና በእችላለሁ መንፈስ በአገር ወስጥ መመረት መቻሉ በስነልቦና ረገድ ለአምራቹም ሆነ ለተገልጋይ ደንበኞች ከፍተኛ ጥቅም እንዳለው ያስረዳል።

አንድ የዳቦ መጋገሪያ ማሽን ከውጭ የሚገባው ከሦስት መቶ ሺሕ ብር (300,000) እስከ አምስት መቶ ሺሕ ብር (500,000) ሲሆን ተመሳሳይ ማሽን በኤልሻሎም ኤሌክትሮ መካኒካል ኢንተርፕራይዝ ተመርቶ የሚሸጠው አንድ መቶ ሃምሳ ሺሕ ብር (150,000) መሆኑንና ለአንድ ዓመት ዋስትና እንዳለው፣ የኤሌክትሪክ ፍጆታቸው በቤት ውስጥ ቆጣሪ እንዲሰራ ተደርጎ የተሰራ ነው፤ ይህ መሆኑ ደግሞ ከተገልጋይ ደንበኞቻቸው መልካም የሆነ የስራ ግንኙነት እንደፈጠረላቸው ይናገራል።



በስራ ሂደት የሚታዩ አንዳንድ የጥራት ችግሮችን ለመፍታትም መንግስት በሚሰጣቸው ስልጠናዎችና ራሳቸውን ለማብቃትና ለማሻሻል በግል ጥረት እያደረጉ እንደሆነ አጫውተውናል።

የሚያመሩቱትን ምርት በማህበራዊ ሚዲያዎችና በክልሉ በሚዘጋጁ ኤግዚቢሽንና ባዛሮችን በመጠቀም በማስተዋወቃቸው ከባህርዳር፣ ከዲላ፣ ከሻሸመኔ፣ ከሆሳዕና፣ ከአርባ ምንጭና መሠል የክልል ከተሞች ደንበኞች እንዳሏቸውና ለተደራሽነት ወሰን መስፋት ዋናው ሚስጢር በጥራት መስራታችን ነው ይላሉ።

አሁን የሚያመርቱትን ተተኪ ምርት የጥራት ሁኔታ ለማሻሻል፣ በብዛት ለማምረትና የፈጠራ ስራዎችን ለመስራት የመስሪያ ማሽን ችግር እንዳለባቸውና ይህን ችግር ለመፍታት ከልማት ባንክ ጋር የማሽን ብድር ለመውሰድ በሂደት ላይ መሆናቸውን ይገልፃሉ።

ሂደቱም ሲጠናቀቅ ችግር ፈች የሆኑ የፈጠራ ስራዎችን በመስራት የበኩላቸውን ሚና ለመወጣት በዝግጅት ላይ እንደሆኑና ለዚህም ሰኬት መንግስት በተለያዩ አግባቦች ተተኪ ምርቶችንና የፈጠራ ስራዎችን ለሚሰሩ ኢንተርፕራይዞች ተከታታይነት ባለው መልኩ ሲደግፍ ነው የሚለው የማህበሩ ሊቀመንበር አምራቹም የሚያመርተው ምርት ጥራቱ የተሻለ እንዲሆን በተለያዩ አግባቦች ራሱን ማሳደግ አለበት ብሏል።

ተጠቃሚው ማህበረሰብም የሚመለከቱትን የጥራት ችግሮች ከአምራቹ ጋር በግልጽ በመነጋገር መስተካከል ያሉባቸውን ከማስተካከል በተጨማሪ በአገር ውሰጥ አምራቾች የሚመረቱ ተተኪ ምርቶች በመግዛት መደገፍ እንደሚገባውቸው፤ ይህ ሲሆን በቀላሉ የአገር ውስጥ ምርቶች በጥራትና በብዛት በማምረት የአገር ውስጥ ገበያ ሆነ የውጨን ገበያ በስፋት መያዝ እንደሚቻል ይናገራል።

አሁን ላይ ማህበሩ አንድ ነጥብ አምስት ሚሊዮን ብር ካፒታል እንዳለውና ለአምስት ወጣቶች የስራ እድል መፍጠር እንደቻሉ፤ በሳምንት እንደ ስራቸው ሁኔታ ለእያንዳንዱ ባለሙያ ከአንድ ሺሕ አምስት መቶ ብር (1,500) እስከ ሁለት ሺሕ ብር (2,,000) ደመወዝ እንደሚከፍሉ ነግሮናል።

ከመንግስት ምንም አይነት ብድር እንዳልወሰዱ የሚያነሳው ወጣት ጋሻው በቀጣይ የጠየቁት የማሽን ብድር ከተሳካላቸው የፈጠራ ስራዎችን በመስራት ተጨማሪ የስራ እድል መፍጠር እንደሚፈልጉ አጫውቶናል።

“አገራችን በግብርናው ዘርፍ የተሻለ እንድትሆን ገበሬው ግዴታ በትራክተር ብቻ ማረስ የለበትም” የሚለው የማህበሩ ሊቀመንበር ሌሎች ቀላል የፈጠራ ስራዎችን በመጠቀም ገበሬው በቀላሉ በማረስ ውጤታማ የሚሆኑበትን የፈጠራ ውጤቶችን በመስራት የአገራችውን ኢኮኖሚ ለማሳደግ እንደ ማህበር በርካታ ስራዎችን መስራት እንደሚፈልጉ አጫውቶናል።

አሁን ካሉበት ደረጃ ለመድረሳቸው በመንግስት በኩል የሚሰጡ ስልጠናዎች በአግባቡ በመሰልጠን ወደ ተግባር መቀየር መቻላቸውና የሚሰሩ ስራዎች በየጊዜው የነበራቸውን የስራ አፈጻጸም በመገምገም ደካማና ጠንካራ ጎኖችን በመለየት ጠንካራውን በማስቀጠል ደካማውን በማስወገድ እንዲሻሻል ማድርግ በመቻላቸው ነው፡፡

ከሌሎች ለየት የሚያደርጓቸው ደግሞ ለማሽን ስራ የሚጠቀሙበት ግብዓት ደረጃውን የጠበቀ መሆኑ፣ ደንበኞች ትዕዛዝ ሲሰጧቸው በተባሉት ጊዜና ስዓት ማስረከብ መቻላቸው ትልቅ ሚና እንደ ነበረው ያነሳው ወጣት ጋሻው ይህን ተሞክሮ ሌሎችም ቢወስዱት ውጤት ማምጣት እንደሚችሉ ጠቁሟል፡፡

"ወጣቱ አገር ለመቀየር በርካታ አቅም አለው፤ ይህ የሚሆነው ደግሞ በስራና በስራ ብቻ ነው፡፡" የሚለው ወጣት ጋሻው ሁሉም ወጣት በተሰማራበት የስራ መስክ ላይ ወጤት ማምጣት የሚችለው የገጠሙትን ችግሮች በትጋትና በብልሀት ማለፍ ሲችል ነው ብሏል፡፡

ችግሮች ሲገጥሙን የምንደነግጥና የምንፈራ ከሆነ ያሰብነውን ማሳካት አንችልም፡፡ በመሆኑም ወደስራ ያልገባ ወጣት ወደስራ በመግባት የሚገጥሙትን ፈተናዎች በአግባቡ በማለፍ እራሱን በመለወጥ አገሩንም ማሳደግ አለበት፡፡

አምራቾችም ቢሆን የሚያመርቱዋቸው ምርት ተወዳዳሪና ድንበር ተሻጋሪ፣ እንዲሁም የአገር ውስጥ ደንበኞችን በሰፊው ለማፍራትና እንዲጠቀሙት ለማድረግ በሚሰጡት አገልግሎት ዙሪያ በየቀኑ ራሳቸውን በማስተማር የተሻለና ጥራት ያለው ምርት ይዘው መቅረብ አለባቸው፡፡

መንግስት የኢንዱስትሪው ዘርፍ ለአገር ኢኮኖሚ ያለውን ከፍተኛ አስተዋፆ በመረዳት በርካታ ስራዎችን በመስራት ላይ እንደሚገኝ የተናገረው ወጣት ጋሻው በመንግስት የግዥ ስርዓት ውስጥ አገር ውስጥ የሚመረቱ ምርቶች መካተት እንዳለባቸው ጠቁሞናል፡፡

የሚሰጡ የብድር አገልግሎቶች ለረጅም ጊዜ የሚከፈል ቢሆን፤ አምራቹን የሚደግፉ ስልጠናዎች ቀጣይነት ባለው መልኩ መስጠት ቢቻል፤ የአገር ውስጥም ሆነ የውጭ አገር የገበያ ትስስር ቢፈጠርልን፤ መሰረተ ልማት ለአምራቹ ማህበረሰቡ ቢሟላለት የሚሉትን ጥያቄ አዘል መልዕክቱንም አስተላልፏል፡፡

ለስራቸው መሳካትና አሁን ላሉበት ደረጃ መድረስ የክልሉ መንግስት፣ የፌዴራል የመንግስት አካላት፣ የማህበሩ አባለት እንዲሁም ለሰራተኞቻቸው ምስጋናውን አቅርቧል፡፡



ልማት

# የኢንተርፕራይዞች ልማት፣ የሐገር በቀል ኢኮኖሚ ግንባታ ወሳኝ አቅም!

አሸናፊ መለሠ

"Let's make the African market be the market for Africans: produce in Africa, transform in Africa, consume in Africa. Let's produce what we need and let's consume what we produce instead of importing. I would not do a fashion show, but I would simply say that we must accept to live as African – that is the only way to live free and dignified.

(ቶማስ ሳንካራ እ.አ.አ በ1987 በአዲስ አበባ ካደረጉት ንግግር የተቀነጨበ)

ሁሉም መንግስት የበለፀገን ሃገር መገንባት ይፈገልጋል፤ ሁሉም ዜጋ የተሻለ ህይወትን ያልማል፤ ሁሉም ትውልድ ለቀጣዩ ትውልድ የሚያወርሠውን ንዋይ ይናፍቃል፡፡

ጥድፊያና ብልጣብልጥነት በሰፈነበት ዓለም ውስጥ ያሠቡትን ሁሉ ለማሳካት የሚችሉ እጅግ ጥቂቶቹ ናቸው፡፡ የእነዚህ ጥቂቶች የስኬት ሚስጥርም አቅምን ታሳቢ ያደረገ ፖሊሲን መንደፍ የቻሉ፣ የተዋጣለት የማስፈፀም አቅምን የገነቡና እንደጊዜና ሁኔታው የሚለዋወጥ ክትትልና ድጋፍን እውን ያደረጉና ሁሉን በሚያሳትፍ፣ ፍትሐዊነት ባመዘነበት የአሠራር ስርዓት ውስጥ ማለፍ የቻሉ ከመሆናቸው ላይ ነው፡፡

እንደኢትዮጵያ ያሉ ታዳጊ ሃገራትም የማደግ ውጥናቸውን ከነባራዊው የዓለም ስርዓት፣ ሀገራዊ ማህበራዊ ሁኔታና ኢኮኖሚያዊ አቅም በመነሳት አዋጪ የሚሉትን የልማት አቅጣጫ ለመከተል መነሳታቸው የሚጠበቅ ነው፡፡

ኢትዮጵያችን ከፍተኛ የህዝብ ቁጥር ካላቸው የአፍሪካ ሀገራት የምትመደብ፣ ከዚህም ውስጥ ከግማሽ በላይ የሆነው በ"ወጣትነት" የእድሜ እርከን ላይ የሚገኝባት መሆኗን፣ የትምህርት ስርዓቷ የሚያምነጨቸውን ምሩቅ ሃይሎች የሚሸከም ጤናማ የስራ ገበያ ያላት አለመሆኗን፣ የስራ አጥነት ጥያቄ ከቁልፍ ማህበራዊና ፖለቲካዊ አጀንዳዎች ተርታ የሚመደብ መሆኑን ከግምት ውስጥ በማስገባትና ሀገራዊ የኢኮኖሚ አቅም ግንባታው ዘላቂነትና ከተፅእኖ ፈጣሪነቱም ሃያል እንዲሆን ለማስቻል ሀገር በቀል የሆነ የኢኮኖሚ ግንባታ አማራጭን መጠቀም ወሳኝ መሆኑን መገንዘብ ካለፉት 3 አመታት ወዲህ ወሳኝ እንቅስቃሰዎችን በማድረግ ላይ ትገኛለች፡፡

ከእነዚህ ሀገራዊ የኢኮኖሚ አቅም መፍጠሪያ አማራጮች ውስጥ ደግሞ በተለይም ለአምራች ዘርፉ ልዩ ትኩረት የሚሠጥ የጥቃቅን፣ አነስተኛና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞችን ማስፋፋት ወሳኝ በመሆኑ ለዚሁ ተልዕኮ ስኬት ራሱን የቻለ መንግስታዊ አደረጃጀት በመፍጠር ወደስራ እንዲገባ ተደርጓል፡፡



# የኢንተርፕራይዝ ልማት ለምን?

አስቀድሞ በመግቢያው ለመግለፅ እንደተሞከረው የጥቃቅን፣ አነስተኛና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች ልማትን ማስፋት እንደኢትዮጵያ ላለ፣ የስራ አጥነት ምጣኔው ከ20 በመቶ በላይ ባሻቀበበትና ሀገራዊ የኢኮኖሚ አቅሙ ውስን በሆነበት ሁኔታ እጅግ ተመራጭ የማህበራዊ ፍትህ ማስፈኛ፣ የኢኮኖሚ አቅም መገንቢያና ወሳኝ የጤናማ የቢዝነስ አቅድ መፍጠሪያ ነው፡፡

ጥናቶች እንደሚያሳዩት ከፍተኛ ገቢ ያላቸው ሃገራት 55 በመቶ የሚሆነውን GDP የሚያመነጩት፣ እንዲሁም 65 በመቶ የሚሆነውን የስራ እድል የሚፈጥሩት በእነዚሁ ኢንዱስትሪዎቻቸው አማካኝነት ነው፡፡

ይህን የስኬት ታሪክ በሀገራችን ተጨባች ሁኔታ ማሳካት ብንችል ብላችሁ አስቡት እንግዲህ!

የኢንተርፕራይዞች ልማት ጥቅም ይሄ ብቻም አይደለም፡፡ ዘርፉ በአንድ በኩል ለስራ ባህል ግንባታ እጅግ የገዘፈ ጠቀሜታ ሲሆነው በዚያውም የመፈፀም አቅምን ለማሳደግ ያለው ሚና "የማይተካ" የሚባለውን አይነት ነው፡፡ በዚህ ላይ እንደግልሠብ ብቻ ሳይሆን እንደማህበረሠብ ጭምር ፈጣን የቢዝነስ ልምምድን ለማምጣት፣ አዳዲስ ሁኔታዎችን ለማላመድና ማህበራዊ ትስስሮሽን ለማጥበቅ ያለው ጥቅም ከልኬትም በላይ ነው፡፡

በጥቂት ካፒታል በርከት ያለ የሠው ሃይልን ወደስራ ያስገባል፤ በቀላል የአስተዳደር ወጪ በርካታና በአንፃራዊነትም ርካሽ ምርቶችን ለማስገኘትም የሚረዳን ይኸው የኢንተርፕራይዞች ልማት ነው፡፡

በሌላ በኩል አዳዲስ የፈጠራ ሃሳቦችን ለማፍለቅ፣ ለማሳደግና ወደችግር ፈቺነታቸው ለማሸጋገር እንደኢንተርፕራይዞች ያለ ምቹ ሁኔታ አይገኝም፡፡

ጤናማ ውድድርን ለመፍጠርና የኢንተርፕርነርሽፕ አመለካከትን በተጨባጭ ለማስፋት እጅግ የተመቸም ነው፡፡

ሌላኛውና ወሳኙ የልማት ዘርፉ ጥቅም በተለይ ሀገራዊና ዓለማቀፋዊ ቀውሶች በሚፈጠሩበት ወቅት ያለ ፈተናን የመቋቋም አቅም ነው፡፡

በተለይ ጠንከር ባለ የአስተዳደርና የአመለካከት አቅም የሚመሩ ኢንተርፕራይዞች ከፍተኛ የሆነ ሀገራዊና ዓለማቀፋዊ ቀውሶች በሚፈጠሩበት ወቅት የሚፈጠርባቸው የጉዳት መጠን ከከፍተኛ ኢንዱስትሪዎች አንፃር እጅግ ዝቅተኛ ነው፡፡

ለዚህም ዋነኛ ምክንያቱ ካለው የሠው ሃይልና ማሽነሪ አቅም የተለዋዋጭነት ባህርይ በመነሳት በቀላሉ የቢዝነስ ዘርፉን በመለዋወጥ በቀውስም ውስጥ ሆኖ ውጤታማ መሆን የሚችሉበትን እድል ለመፍጠር በመቻሉ ነው፡፡

ለአብነት የኮቪድ ወረርሽኝ ከፍተኛ ስጋት በነበረበትና ሀገራዊ የቢዝነስ እንቅስቃሴ በተዳከመበት ወቅት በጨርቃጨርቅ፣ ቆዳ፣ ኬሚካልና ብረታብረት ዘርፍ የተሠማሩ የተወሠኑ አምራቾች ሀገራዊ የቢዝነስ ሁኔታውን ተከትለው ሠራተኞቻቸውን ከመበተንና ማምረቻዎቻቸውን ከመዝጋት ይልቅ የተለያዩ የአፍ መሸፈኛ ማስኮችን፣ የእጅ መታጠቢያ ሳሙናዎችን፣ ሳኒታይዘር፣ ከእጅ ንክኪ የሚያርቁ የእጅ መታጠቢያና ሳኒታይዘር መርጫ መሳርያዎችን በማምረት በሀገራዊው የቀውስ ወቅት ውጤታማ የስኬት ጊዜያትን ለማሳለፍ ችለዋል፡፡

ከዚህም በላይ በጥሬ እቃ አቅርቦት፣ በአምራች፣ አከፋፋይና ቸርቻሪ የገበያ ሠንሠለትና መሠል ተያያዥ የእሴት ሠንሠለቶችን በመፍጠር በርካታ የማህበረሠብ ክፍሎችን ተጠቃሚ ለማድረግ የሚያስችል የቢዝነስ አውድንም ይፈጥራል፡፡

# ስለዚህ ለዘርፉ ስኬት ኢትዮጵያ ምን ታድርግ?

በተሞክሮ ደረጃ ኢትዮጵያ ለዘርፉ ልማት አዲስ አይደለችም፡፡ ከ1934 ዓ.ም ጀምሮ የ"አነስተኛ እደጥበብ" ሙያዎችን የማስፋፋት፣ የ"ጎጆ" ኢንዱስትሪዎችን የማላመድና ለዘርፉ በልዩ ትኩረት የሚሠጡ ድጋፎችን የማመቻቸትና የማሳለጥ ስራዎች ሲከናወኑ ቆይተዋል፡፡

እነዚህ ጥረቶች በበርካታ ስኬቶች የመታጀባቸውን ያህል በዚያው ልክ በውስብስብ መሠናክሎችም የታጠሩ ነበሩ፡፡ በመሆኑም በየወቅቱ የሚታዩ የዘርፉን ችግሮች ለማስወገድ በርካታ ጥረቶቹን ሲያደርግ ቆይቷል፡፡

እነዚህ ጥረቶች ከሞላ ጎደል በፖሊሲ መንደፍ፣ በመዋቅራዊ አደረጃጀት ማሻሻያዎች፣ በአሠራር ዝርጋታዎችና በአቅም ግንባታ ስራዎች የሚገለፁ ናቸው፡፡

መንግስት እነዚህን ሂደቶችና ሂደቶቹ ያመጧቸውን ስኬቶችና ድክመቶች ታሳቢ ባደረገ አግባብ ዘርፉን በተሻለ መንገድ ለመደገፍና ለመምራት የሚያስችል አዲስ አደረጃጀት ፈጥሯል፡፡



ይህ አደረጃጀትም "የኢትዮጵያ ኢንተርፕራይዝ ልማት" በሚል ስያሜ ከጥቃቅን እስከመካከለኛ ኢንተርፕራይዞችን ለመደገፍ ያለመ ነው። በዚህም በዋናነት ለአምራች ዘርፉ ልዩ ትኩረት በማድረግ የሚሠራ ይሆናል።

ይህን ግዙፍ ሐላፊነት በተሻለ አግባብ ለመምራት፣ ከዚህ በፊት ሲስተዋሉ የነበሩ መሠረታዊ ችግሮችን ለመቅረፍና ከዘርፉ ሊገኝ የሚችለውን አቅም በሙሉ አሟጦ ለማግኘት እንዲቻል ካሁኑ በርካታ ስራዎችን መስራት ያስፈልጋል።

የመጀመርያው ተግባር የግንዛቤ ማስጨበጥ ስራ ነው። በዘርፉ ውስጥ ተዋናይ የሆኑ አስፈፃሚ፣ ፈፃሚና መሠል ባለድርሻዎች ሁሉ ስለዘርፉ የጠራ ግንዛቤ ሊኖራቸው ይገባል!
ገብቶት፣ አምኖበትና አውቆት የሚመራ አስፈፃሚን መፍጠር ከተቻለ የሚንጠባጠብ አፈፃፀም፣ የሚበታተን ትኩረት፣ ያልተቀናጀ እንቅስቃሴ አይኖርም።

ሁኔታውን በወጉ የተረዳ ፈፀሚን መፍጠር ከቻልን በዓለማቀፍ ተሞክሮዎች የበለፀገ፣ ሳይንስን የተተገነና በሐላፊነት የተሞላ አገልግሎትን ለመስጠት የሚያስችለንን የስራ ሁኔታን ገነባን ማለት ይሆናል።
የነጠላ ኢንዱስትሪዎች ድምር ውጤት በሐገራዊው የኢኮኖሚ ግንባታ ላይ የሚያዋጣውን ተዓምራዊ አቅም የተገነዘበ የኢንተርፕራይዝ ባለቤት ለሚያስፋፋው የመስሪያ ቦታ፣ ስለሚቀጥራቸው ተጨማሪ የስራ እድሎችና ስለሚያሳድገው የገበያ ተደራሽነቱ መድከሙ አይቀርም።

የተቀናጀ ስራው የሚፈጥረውን ሐገራዊ ተዓምር በአግባቡ የተረዳ የፋይናንስ፣ የጥሬ እቃ፣ የማምረቻ ማሽን አበዳሪ፣ የመስሪያ ቦታ አመቻችም ሆነ የቴክኒክ ክህሎትና የጥናትና ምርምር አቅራቢ ተቋም የድጋፍ አትኩሮቱን ቅኝት አስተካክሎ እንደአቻዎቹ ተመሳሳ ቋንቋን እያወራ ለዘርፉ እድገት ደፋ ቀና ማለቱ ይጠበቃል።

በመሆኑም ለአንድ ዓላማ የሚሠባሠበው በየደረጃው የሚገኝ የዘርፉ ተዋናይ በተመሳሳይ የግንዛቤ ቅኝት እየታገዘ ተልዕኮዎችን መፈፃምና ማስፈፀም እንዲችል የግንዛቤ ፈጠራው መቅደም አለበት።

ህብረተሠቡም በዘርፉ በስፋት መሠማራት እንዲችል፣ በዘርፉ የተሠማሩ ዜጎችን እንዲደግፍና በሀገር ውስጥ ምርቶች የመጠቀም ባህሉን እንዲያሳድግ ማሳመን፣ ማነሳሳትና ለዚህም ስልቶችን ነድፎ መንቀሳቀስ ያስፈልጋል።

ሌላኛው ጉዳይ ዘርፉን በሳይንስና በበለፀገ የተሞክሮ አቅም ለመምራት (እና ለመፈፀም) መቻል ነው።

እንደመታደል ሆኖ የኢንተርፕራይዞች ልማት በሀገርም ሆነ በዓለም አቀፍ ደረጃ አዲስ ነገር አይደለም። በዓለም ዓቀፍ ደረጃ እ.አ.አ ከ1960ዎቹ ጀምሮ በስፋት ሲሠራበት የነበረ ነው።

በእነዚህ ዓመታትም በዘርፉ እጅግ የተሳካላቸው፣ ያልተሳካላቸውና ጨራሹኑ ዘርፉንም ዘር ብለው ያላዩ ሀገራት ይኖራሉ።

ሌላኛው ጉዳይ ዘርፉን በሳይንስና በበለፀገ የተሞክሮ አቅም ለመምራት (እና ለመፈፀም) መቻል ነው። እንደመታደል ሆኖ የኢንተርፕራይዞች ልማት በሀገርም ሆነ በዓለም አቀፍ ደረጃ አዲስ ነገር አይደለም።

በዓለም ዓቀፍ ደረጃ እ.አ.አ ከ1960ዎቹ ጀምሮ በስፋት ሲሠራበት የነበረ ነው። በእነዚህ ዓመታትም በዘርፉ እጅግ የተሳካላቸው፣ ያልተሳካላቸውና ጭራሹኑ ዘርፉንም ዘር ብለው ያላዩ ሀገራት ይኖራሉ።

በመጨረሻም፡-

ፈረንጆች "ሮም በአንድ ቀን አልተገነባችም" ይላሉ። (እኛም "ቀስ በቀስ እንቁላል በእግሩ ይሄዳል" እንላለን) አባባሎቹ በአንድ ጀንበር ተጠንስሶ በአንድ ጀንበር ውጤቱ የሚታይ ስኬት አለመኖሩን የሚያመላክቱ ናቸው።

ሐገራችን የኢንተርፕራይዝን ልማት ለ80 ዓመታት ታውቀዋለች ብንልም ዘርፉን በሳይንስ አስደግፎ፣ ስትራቴጂ ቀርፆና ወሳኝ አደረጃጀት ፈጥሮ መምራት የተጀመረው በቅርቡ ነው።

ከዚሁ "ቅርብ" ውስጥም ዘርፉን የፖለቲካ ትኩሳት ማብረጃ በማድረግ ለዘርፉ ልማት ከመረባረብ ይልቅ በስሙ የመነገድ ሁኔታ የታየበትም ዘመን ነበር።

በመሆኑም ይህን ዘመን በአግባቡ መጠቀም ታሪካዊ ሐላፊነታችን ነው። እንደሐገር ለዘመናት አብሮን የቆየውን ድህነት የምንቀርፈው፣ ድህነታችን የፈጠረብንን "የምዕራባውያን ተፅእኖ ማረፊያነት" የምንሠብረው የኛ የምንለውን ኢኮኖሚ መገንባት ስንችል ነው።

ለዚህ ደግሞ የኢንተርፕራይዝ ልማቱ ሐገር በቀል የኢኮኖሚ ግንባታ ሕልማችንን መሠረተ ሠፊ፣ ፍትሐዊ ተጠቃሚነትን ያረጋገጠ፣ ያለንን ውስን ሐብትና ሠፊ የሠው ሃይል ተሸክሞ የሚያሻግረልን ወሳኝ መፍትሔ በመሆኑ ለዘርፉ ስኬት ባለን አቅም ሁሉ ልንረባረብ ይገባል!

ስዋሚ ቨቪቨካናንዳ የተባለ ሕንዳዊ ቄስና ፈላስፋ በአንድ ወቅት "ሁሉም ሀገር ሊነግረው የሚፈልገው መልዕክት፣ ሊያሳካው የሚፈልገው ተልዕኮና ሊደርስበት የሚሻው መገኛ አለው፤ የሕንድ ተልዕኮ



# ኢ-ኮሜርስ ለኢንተርፕራይዝ ልማት ያለው ፋይዳ

## በገበያ ልማትና ኢንዱስትሪዎች ትስስር ዳይሬክቶሬት

### መግቢያ

እንደኢትዮጵያ ባሉ ታዳጊ ሀገራት የጥቃቅን፣ አነስተኛና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች ለማክሮ ኢኮኖሚ የሚያበረክቱት አስተዋጽኦ ወደር የለውም፡፡

እነዚህ ተቋማት ለሥራ ዕድል ፈጠራ፣ ተመጣጣኝ ዋጋ ያለው ሸቀጥ ለማቅረብ፣ የሀገር ውስጥ ገቢ ለመጨመርና የውጭ ምንዛሬ ግኝትን ለማሳደግ ሚናቸው የጎላ ነው፡፡ በመሆኑም የአነስተኛና መካከለኛ ኢንተርፕራይዝ ልማትን ማጎልበት ለነገ የሚባል ስራ መሆን የለበትም፡፡ ኢንተርፕራይዞች የገበያ ልማታቸው እንዲያድግ የቴክኖሎጂ እና የዲጅታል ግብይት መሠረተ-ልማት ማልማቱ ጊዜውን የዋጀ የድጋፍ ስራ ነው፡፡

የኢንፎርሜሽን ቴክኖለጂ ለጥቃቅን፣ አነስተኛና መካከለኛ ኢንተርፕራይዝ የገበያ ልማት ፋይዳው ዘርፈ-ብዙ ነው፡፡ በቴክኖሎጂ በመጠቀም ከመላው ዓለም በመገናኘት በአጭር ጊዜ ውስጥ ድንበር ሳይገድብ የግንኙነት አድማስን በማስፋት የኢንተርፕራይዙን የኢኮኖሚ፣ የቴክኖሎጂ እና የግብይት ማደግንና መዘመንን ይፈጥራል፡፡

ኢ-ኮሜርስ የንግድ መዳረሻቸውንና የሽያጭ መጠናቸውን በመጨመርና ወጪያቸውን በመቀነስ እንዲሁም የንግድ መቀላጠፍን በመጨመር በኩል የሚያበረክተው አስተዋጽኦ ወደር የለውም፡፡ የኢንተርፕራይዝ ልማት ግዙፍ ተዕልኮን በብቃት ለመወጣት ብቃት ያለው የኢ-ኮሜርስ ሥርዓትን መከተል ወሣኝ ነው፡፡

ትክክለኛ የኢኮሜርስ የድጋፍ ማዕቀፍን በተገቢው ማደራጀትና ጥቅም ላይ ማዋል ከዘርፉ ዕድገት ጋር ቀጥተኛ የሆነ ቁርኝት እንዳለው ሁሉ ጥራቱን ያልጠበቀና ነባራዊ እውነታውን ያላገናዘበ የድጋፍ ማዕቀፍ ውጤቱ ወደ የተሳሳተ መደምደሚያ ይወስዳል፡፡ትክክለኛ የኢኮሜርስ የድጋፍ ማዕቀፍን በተገቢው ማደራጀትና ጥቅም ላይ ማዋል ከዘርፉ ዕድገት ጋር ቀጥተኛ የሆነ ቁርኝት እንዳለው ሁሉ ጥራቱን ያልጠበቀና ነባራዊ እውነታውን ያላገናዘበ የድጋፍ ማዕቀፍ ውጤቱ ወደ የተሳሳተ መደምደሚያ ይወስዳል፡፡





## የኢኮሜርስ ሁለንተናዊ ትርጉም

እንደዘርፉ ምሁራን ብያኔ ኢ-ኮሜርስ የኮምፒውተር አውታርን በመጠቀም በደንበኞች መካከል የሚደረገውን የመግዛት፣ የመሸጥና በአጠቃላይ የንግድ ልውውጥ ሂደትን ነው:: በሌላ በኩል ደግሞ ኢ-ኮሜርስ የቴሌኮሚኒኬሽን ኔትወርክን በመጠቀም የመረጃና የንግድ ልውውጥ ድጋፍ በደንበኞችና በአቅራቢዎች መካከል የሚደረግ አገልግሎት ነው።

ኢ ኮሜርስ የንግድ ግንኙነት መድረክ ሲሆን በደንበኞች፣ በንግድ ሼሪኮች፣ በሠራተኞችና አቅራቢዎች መካከል ኢንተርኔትን በመጠቀም የግንኙነት ዕድልን መፈጠርም ነው።

በአጠቃላይ ከላይ ከተዘረዘሩት ብያኔዎች የምንረዳው ኢ-ኮሜርስ ምርትን፣ አገልግሎትንና ሌሎች ተግባራትን የኤሌክትሮኒክስ የተቀናጀ ሚዲያን በመጠቀም የሚፈጠር ምቹ የንግድ ልውውጥ ከባቢ የሚፈጥር መሆኑን ነው።

ይህንኑ ምቹ ከባቢ ለኢንተርፕራይዞች በሚያመች መልኩ በማልማት መጠቀም መቻል ለዘርፉ፣ ለሀገር እና የኢንተርፕራይዝ ልማትን ለማሳለጥ ከፍተኛ ሚና አለው።

## ከኢ-ኮሜርስ የሚገኝ ጥቅም

ኢ-ኮሜርስ ለጥቃቅን፣ አነስተኛና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች ብዙ ፋይዳዎች አሉት።

እንደሚታወቀው በዚህ የስራ ዘርፍ ያሉ ኢንተርፕርይዞች በብዛትና በስፋት የሽያጭ አውታሮችን በማስፋፋት እስከ ታችኛው የምርትና የአገልግሎት ተጠቃሚ ለማድረስ የፋይናንሻል አቅም፣ የአስተዳደር ችሎታና ሌሎች ተግዳሮቶች እንደልባቸው አያንቀሰቅሳቸውም።

ሌላው ደግሞ በየቦታው ለሚከፍቱት መሻጫና ማሳያ ቦታ ኪራይ፣ የሚቀጥሩት የሰው ኃይል ወጪ ሌላው አቅምን የሚፈጥር ጉዳይ በመሆኑ ኢ-ኮሜርስ የሚከተሉት ዋና ዋናዎቹን ጥቅሞች አሉት።

### ሀ. የኢንተርፕራይዙን ወጪ ይቀንሳል

- የግብይት ወጪን ይቀንሳል(Marketing cost)
- የንግድ ልውውጥ ወጪንን ይመጥናል (Transaction cost)
- የመሸጫና የማሳያ ኪራይ ወጪ መቀነስ ( Selling premises cost)

- የሠው ኃይል ቁጥር ይቀንሰል።

እነዚህንና ሌሎችበዚህ በላይ ያልተጠቀሱ ወጪዎችን በመቀነስ ግብይቱን ቀልጣፋ፣ ተደራሽ እና ዘመናዊ በማድረግ የኢንተርፕራይዙን ተጠቃሚነት ያሳድጋል

### ለ. የኢንተርፕራይዙን ትርፋማነት ይጨምራል

- ደንበኛን ይጨምራል፤
- በቀላሉ በብዙ ቦታዎች ተደራሽ መሆን ይችላል፤
- ለእያንዳንዱ ደንበኛ ምርትና አገልግሎቱን ለማስተዋዋቅ ይረዳል፤

### ሐ. የገበያ ድርሻን (Market Share) ያሳድጋል፤

### መ. የገበያ ሂደትን ያቀላጥፋል፤

### ሠ. የደንበኞችን አገልግሎት ያቀላል፤

### ሸ. የኤክስፖርት ገበያን ያበረታታል፤

### በ. የንግድ ልማትን ጊዜ ይቆጥባል፤

- ደንበኛ ለመፈለግ የሚጠፋ ጊዜን፣
- በየስርጭት ቦታዎች የሚደረግ የሱፐርቪዥን ጊዜን፣ለማስተዋዋቅ ይረዳል፤
- በየመዳረሻ ቦታዎች ምርትና አገልግሎት ለማድረስ የሚፈጅን ጊዜ እና ለሌሎች ጉዳዮች የሚያጠፉትን ጊዜ በአንድ ውስን ቦታ በመሆን በቨርቸዋል ግንኙነትን በማጠናከር የሚፈለገውን አገልግሎትና ምርት በማቅረብ የተሻለ ኢንተርፕራይዝ ያደርጋል።

በድምሩ ኢ-ኮሜርስ የኢንተርፕራይዞችን ዓለምአቀፋዊነት ግንኙነትን በማስፋት በዓለም አቀፍ ደረጃ ትልቅ ዕድል በማስፋት በዚያው ልክ ተወዳዳሪነትንና ተጠቃሚነትን ያሳድጋል።

በዓለም አቀፍ ደረጃም የሚደረጉ ግብይቶችን በማቃለል፣ የግብይት ወጪን በመቀነስ እና የንግድ ሂደቱን በማቀላጠፍ ረገድ የሚያበረክተው አስተዋጽኦ ከፍ ያለ ነው።

በተለይም በዓለም ደረጃ በዲጂታል ማስታወቂያዎቹ ለመቶ ሺዎች፣ ለሚሊዮኖች እና ለቢሊዮኖች መድረስ የሚያስችል ሥርዓት በመሆኑ በተለይም ለጥቃቅን፣ አነስተኛና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች ተመራጩ የንግድ ስልት ነው።

ጭምር በቀላሉ መጠቀም የሚያስችለን በመሆኑ በተለይ የኢንተርፕራይዞችን የንግድ ይህንኑ ዘዴ መጠቀም ጊዜና ቦታ የማይገድበው በመሆኑ ባለንበት ቦታ ሆነን ስማርት ስልኮችን ሂደት የሚያሳልጥ ቴክኖሎጂን በመተዋዋቅ መጠቀም ለነገ የሚባል ጉዳይ አይሆንም።

ኢ-ኮሜርስን ለንግድ ስራ በአግባቡ መጠቀም በጥሩ መሬት ላይ የተዘራን ከአስተማማኝ ምንጭ በሚዘልቅ የመስኖ መስመር የሚጠጣን አትክልት ይመስላል። ለንግድ ስራም የዘመኑን ኢኮሜርስ ቴክኖሎጂ መጠቀም ተከታታይና ዘላቂ የገበያ ልማት ዕድል ከመፈጠሩም ባሻገር በዓለም አቀፍ ደረጃ የኢንተርፕራይዝ ተወዳዳሪነትን ይጨምራል።

የኢንተርፕራይዞችን ተዓማኒነት እንዲሁም ከደንበኞች ዘንድ ዘመናዊነትን ይጨምራል።

በጥቅሉ ኢንተርፕራይዞች ኢ-ኮሜርስን በመጠቀም ንግዳቸውን ከማቀላጠፍ አልፎ የዘርፋን ምርታማነትና ውጤታማነት ይጨምረዋል። ይህን ዓለም የሚያዩበት መንገድ በማስፋትም ዓለም አቀፋዊ ተወዳዳሪነትን ይጨምራል።

## ኢ-ኮሜርስን ለመተግበር የሚያጋጥሙ እንቅፋቶች

በሀገራችን የኢንተርፕራይዝ ልማትን ለማፈጠን የኢንተርኔት ቴክኖሎጂ ማበልጸግ ወሳኝ ነው። የበለጸገውንም ቴክኖሎጂ ለመጠቀም በክህሎት የዳበረ የሠው ኃይል ያስፈልጋል።

ይህን ሁኔታ ውጤታማ ለማድረግ ደግሞ የተሳለጠና ተደራሽ፣ ዘላቂነት ያለው የኢንተርኔት መሠረተ-ልማት ይጠይቃል።

በዋናነት ዋና ዋና የኢ-ኮሜርስ እንቅፋቶች የሚከተሉት ናቸው።

### ሀ. ደካማ የኢንተርኔት አገልግሎት

በሀገራችን የኢንተርኔት መሠረተ-ልማት ዝርግታው በሁሉም አከባቢዎች ተደራሽ አይደለም። የተዘረጋውን መሠረተ-ልማት በግንዛቤ እጥረት፣ በግል ተራ ፍላጎቶች መስገብገብና እና ሌሎችም አሉታዊ ተግባሮች ምክንያት በዘላቂነት አገልግሎት በማይሰጥበት ሁኔታ የሚቆረጥበት ጊዜም አለ።

በሌላ በኩል ደግሞ የውሃ፣ የመንገድና የመብራት መሠረተ-ልማቶች ሲዘረጉ ተገቢውን ጥንቃቄ ባለመደረጉ በኬብሎች ላይ የመቆራረጥ አደጋ ያጋጥማል።

በሀገራችን ደካማ የኢንተርኔት አገልግሎት በመኖሩ ምክንያት ከቀበሌ ጀምሮ ያሉትን ግንኙነቶች አጠናክሮ የተሻለ የኢ-ኮሜርስ ንግድ ሥርዓት በሚፈለገው ደረጃ በማድረስ የሚፈለገውን ውጤት በማምጣት የኢንተርፕራይዞች ተጠቃሚነት ለማረጋጋጥ ዋና ማነቆ እንደሆነ ይታመናል።

### ለ. በኢ-ኮሜርስ ላይ የቴክኒካል የክህሎት እጥረት መኖር

ኢ-ኮሜርስ በአይሲቲ ቴክኖሎጂ ላይ ክህሎት ያለው፣ በዘርፉ በቂ ግንዛቤ የፈጠረ፣ ለዓለምአቀፋዊ ግንኙነት በቂ ዕውቀት ያለው፣ በጥቅሉ ብቃት ያለውን የሠው ኃይል መፈጠር ይፈልጋል።

በዚህ ረገድ በኢንተርፕራይዝ ልማት ላይ በኢ-ኮሜርስ አጠቃቀም ብቃት ያለው የሠው ሃይል ተፈጥሮ ተገቢውን ድጋፍ የሚሰጥ የመንግስት፣ የአጋር እና በጎ አድራጎት ተቋማት እምብዛም በሀገራችን አይታዩም።

በዚሁ ምክንያት የኢ-ኮሜርስን አገልግሎት በተግባር ወደ ስራ ሊያስገባ የሚችል አደረጃጀት፣ የአሠራር እና የድጋፍ ማዕቀፍ አልታየም።

በእርግጥ አልፎ አልፎ በግልና በተናጠል ተቋማትና ግለሰቦች ብቅ እልም እያሉ በሥልጠና መልክ የኦረንቴሽን ዓይነት ድጋፎች ይሞክራሉ። በዚህ ዓይነት በተበጣጣሰ አካሄድ የዘርፉን ኢ-ኮሜርስ የክህሎት፣ የዕውቀትና የአመለካከት በአጠቃላይ የብቃት ማነስን መቅረፍ ያስፈልጋል።

### ሐ. በኢ-ኮሜርስ ላይ የህብረተሰቡ እምነት ማነስ

ይህ አገልግሎት በሌላው ዓለም ከፍተኛ የሆነ ግብይት የሚፈጸምበት አውታር ነው። በሌላው ዓለም ይቅርና ጎረቤቶቻችን ዲጅታል ቴክኖሎጂን በመጠቀም የንግድ እንቅስቃሴቸውን ማቀላጠፋቸውን ከሚወጡ የፋይናንሻል ሪፖርቶች መረዳት ይቻላል።

በሀገራችን በመንግስት ደረጃ የዲጅታል ፖሊሲ፣ ስትራቴጂና የማስፈጸሚያ የህግ ማዕቀፎች ቢቀረጹም በቂ ግንዛቤ በህብረተሰቡ ላይ አልተፈጠረም።

በዚህ መነሻ የሀገራችን የግብይት ሁኔታ በተለመደው ባህላዊ አሰራር የሚደረግ በመሆኑ የኢ-ኮሜርስ ግብይትን እንደ ቅንጦት ይቆጠራል።

ከምንም በላይ በአገልግሎቱ ላይ እምነት የሚፈጥር የፖሊሲ ማዕቀፍ አሰራር ባለመዘርጋቱ በኃላፊነት ሥራውን የሚመሩና የሚያስፈጽሙ አካላትም በውል ጎልተው ባለመውጣታቸው ህብረተሰቡ ኢኮሜርስ ላይ በቂ እምነት እንዲኖረው አልተደረገም።



አንዳንድ የዲጅታል ተቋማት ብቅ ብሉ ሲሉ ብዙ ጊዜ የሚነሳው የእምነት ጉዳይ ነው። በተለይም የክህሎት ሁኔታ፣ ምርቱ ተደራሽ የሚሆንበት ሁኔታ ላይ የቀረበው አገልግሎት ወይም ምርት በሚፈለገው ደረጃና ጥረት ባይኖርው የዋስትና ጉዳይ እንዴት ይስተናገዳል የሚሉ የሚሉ ጥያቄዎች ይነሳሉ።

በሀገራችን የኢንተርፕራይዞችን የገበያ ከባቢያዊ ሁኔታዎችን ማመቻቸት ካልተቻለ እና ኢ-ኮሜርስ ላይ እምነት ፈጥረው ግብይታቸውን ማቀላጠፍ ከልተቻለ በሚፈለገው ልክ የኢንተርፕራይዝ ልማቱን ማቀላጠፍ ያስቸግራል።

## ኢኮሜርስን ለኢንተርፕራይዝ ልማት ለማበልጸግ ማን ምን ያድርግ?

### ሀ. ዩኒቨርስቲዎች እና የስልጠና ተቋማት ለኢንተርፕራይዞች የገበያ ልማት በሚጠቅም መልኩ የኢ-ኮሜርስ ፕላት ፎርም ማዘጋጀት

መረጃ የኢንተርፕራይዞችን ኢኮኖሚያዊ፣ ማሕበራዊና አጠቃላይ ሁለንታናዊ ገጽታዎችን ማሳየት፣ መረዳትና መገንዘብ የሚቻለው በሚገባ የተሳለጠና ውጤታማ የገበያ ልማትና የኢ-ኮሜርስ ቴክኖሎጂ በአግባቡ ሲዋቀር ነው።

ለዚህ ደግሞ የትምህርትና ስልጠና ተቋማት በየአካባቢያቸው ለሚሰሩ ኢንተርፕራይዞች ሊጠቅም የሚችል ሶፍትዌሮችን በማልማት፣ ተገቢውን ስልጠና በመስጠትና ግንዛቤ በመፈጠር የኢንተርፕራይዞችን የገበያ ልማት ማቀላጠፍ ያስፈልጋል፡፡

ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት የኢንተርፕራይዞችን ችግር ለማቃለል መስራት ማህበራዊም ሆነ የሞራል ግዴታቸው ነው፡፡ በመሆኑም በዘላቂነት ለገበያ ልማት ሊውል የሚችል የኢ-ኮሜርስ ቴክኖሎጂ ስርዓት የሚለማበትን ሁኔታ ማመቻቸትን ይጠይቃል፡፡

### ለ. ዘርፉን የሚደግፉ አካላት በጋራ አቅደው የኢንተርፕራይዞች የኢ-ኮሜርስ ተጠቃሚነትን ማሳደግ

ሀገር አቀፍም ሆነ ዓለም አቀፍ ድርጅቶች ለሚያደርጉት የኢንተርፕራይዝ ልማት ድጋፍ፣ በተለይም የቴክኖሎጂ ድጋፉ ለኢንተርፕራይዞች ተጨባጭ ውጤት በሚያመጣ መልኩ ሊያደርጉ ይገባል፡፡ አብዛኛዎቹ የኢንተርፕራይዝ ልማት አጋር ተቋማት ትኩረት የሚያደርጉት በንድፈ ሐሳብ ስልጠናዎች ላይ ነው፡፡

ነገር ግን የኢንተርፕራይዞችን የገበያ ልማት ሊያሳደግ፣ ንግዱን ሊቀላጥፍና የአምራች ኢንዱስትሪውን የኤክስፖርት ገበያ ዕድል ሊያሳድግ የሚችል የቴክኖሎጂ ድጋፍ ያስፈልጋል፡፡ የኢንተርፕራይዝ ልማቱን እንደግፋለን የሚሉ በርካታ የሀገር ውስጥና የውጭ ሀገር አጋር ድርጅቶች ኢንተርፕራይዙ የኢ-ኮሜርስ ቴክኖሎጂን በመጠቀም የገበያ ዕድሉን ማስፋት የሚያስችል ተግባራዊ ድጋፍ ማድረግ አለባቸው፡፡

### ሐ. የዘርፉን ልማት የሚያስፈጽሙ አካላት የኢ-ኮርሜርስ የድጋፍ ማዕቀፍ መቅረጽ

ከፌደራል መንግስት እስከ ታችኛው የወረዳ እርከን ድረስ ያለ የዘርፉ መዋቅር ኢ-ኮሜርስን መጠቀም ለኢንተርፕራይዝ ልማት ዘርፈ-ብዙ ችግር የሚያቃልል ዘመናዊ አሰራር መሆኑን በቂ ግንዛቤ መያዝ ይጠበቅባቸዋል፡፡

በየደረጃው የሚገኙ አካላት በተጨባጭ በኢንተርፕራይዝ ልማት ላይ ውጤት ማምጣት ከፈለጉ የዚህን ቴክኖሎጂ ጥቅም በመረዳት በኢንተርፕራይዝ ልማት ውስጥ የኢ-ኮሜርስ ቴክኖሎጂ ድጋፍ በፖሊሲ፣ በስትራቴጂና በህግ ማዕቀፎች ውስጥ ተካቶ እንደአንድ የድጋፍ ማዕቀፍ ተቀርጾ የድጋፉ አካል መሆን አለበት፡፡

ይህ ሲሆን የኢንተርፕራይዞች ዘመናዊነት፣ ከአንዱ ወደ ሌላው ደረጃ የሚያደርጉትን ሽግግር እና ዕድገት ፈጣንና የሚታይ ይሆናል፡፡ የዘርፉን የመረጃ ፍሰት፣ ተደራሽነት፣ ጥራትና የአገልግሎቱን መቀላጠፍ ያሳድገዋል፡፡

### መ. ኢንተርፕራይዞች በኢ-ኮሜርስ ላይ ያላቸውን ዝቅተኛ አመለካከት ማስወገድ

አሁን ያለንበት ዘመን ዓለምን አንድ በማድረግ በአይሲቲ ቴክኖሎጂ የተሳሰረ በመሆኑ በአንድ መንደር የሚኖር ያክል አቀራርቧል፡፡

ይህ መልካም ዕድል ያለውን ያክል የውድድር አድማሱን በማስፋት የገበያ ዕድሎች ላይ የሚፈጠረው አሉታዊ ተጽእኖ ቀላል አይደለም፡፡

ይህንን በመረዳት ‹‹በሰነፍ ቀዬ ሞፈር ይቆረጣል!›› እንዲሉ ከዕድሉ ለመጠቀም ተግባራዊ እንቅስቃሴ ማድረግ ይጠበቃል፡፡

በሀገራችን የሚገኙ ኢንተርፕራይዞች የንግድ ክህሎታቸው እና የገበያ ልማታቸውን ለማበልጸግ ከፈለጉ የኢ-ኮሜርስ ቴክኖሎጂ ላይ በቂ የሆነ ተነሳሽነት፣ ዕቅድና ክህሎት ማሳደግ ይጠበቅባቸዋል፡፡

ኢ-ኮሜርስ የንግድ ልማታቸውን ሊያሳድግ የሚችል የቴክኖሎጂ አውድ መሆኑን በመረዳት ለተግባራዊነቱ ስልጠና፣ የቴክኖሎጂ ቁሳቁሶችንና የቴኮሎጂ መሠረተ-ልማት የሚያገኙበትን ሁኔታ ማመቻቸት ያስፈልጋል፡፡

ኢንተርፕራይዞች ኢ-ኮሜርስ በስራቸው ላይ የሚፈጠረውን በጎ ውጤት በማጤን ተጠቃሚ ለመሆን ግንባር ቀደም ተዋናይ መሆን ይገባቸዋል፡፡



## መዝናኛ

አንድ ጊዜ በጣም ስኬታማ የሆነች ሴት ሚስጥሯን እንድታካፍለኝ ጠየኳት።
ፈገግብላ እንዲህ አለችኝ...
"እኔ ስኬታማ መሆን የጀመርኩት ትናንሽ ትግሎችን ለትናንሽ ታጋዮች መተው ስጀምር ነው።
ሀሜተኛ የሆኑብኝን መጣላት አቁሜያለሁ...
ከጠላቶቼ ጋር መጣላት አቁሜያለሁ...
ትኩረት ለማግኘት መታገል አቁሜያለሁ...
ሰዎች ስለእኔ የሚጠብቁትን ነገር ለማሟላት መታገል አቁሜያለሁ...
ሁሉንም ሰው ለማስደሰት መታገሌን አቁሜያለሁ...
ስለኔ ትክክል እንዳልሆኑ ለማሳየት ትግሌን አቆምኩ...
እንደዚህ አይነት ሙግቶችን ሌላ ጠብ ስለሌላቸው ተውኩት...
እናም ለራዕዬ፣ ለህልሜ፣ ለሀሳቤ እና ለዕጣፈንታዬ መታገል ጀመርኩ።
አንዳንድ ግጥሚያዎች ጊዜህን አይመጥኑም.....
የምትታገልለትን ነገር በጥበብ ምረጥ!"
#ችግር_የለውም_ችግር_አለው!

አይንህን ገልጠህ ተጠባበቅ። እናም አንድ ትንሽ ችግር ሲገጥምህ ወዲያውኑ ጠግነው። አይ ችግር የለውም አትበል።
ነገሮች መስመራቸውን በሳቱበት ቅጽበት ለማስተካከል ሞክር።

ህይወት በእጅጉ ከባድ፣ አንዳንዴ ለመቋቋም እስኪያቅትህ ድረስ አስቸጋሪ ናት። እናም ይህን ስታውቅና ለስቃይህ ምክንያት የሆኑ ነገሮች ስትለይ መፍትሄን ማምጣት ትችላለህ።
ስቃይህ እንዲያዳክምህ ከሰውነት ተራ እንዲያወጣህ አትፍቀድለት።

ደጋግመህ ስታማርር ነገሮችን ታብሳቸዋለህ እንጂ አታስተካክላቸውም። ለገጠመህ ችግር መፍትሄ የምትፈልግበት መንገድ እንጂ ስቃዩን የምታባብልበት ሁኔታ አይኑር።

በሙሉ እምነትም ወደፊት መጓዝና መጋፈጥ ስትጀምር ብቻ ታሸንፋለህ።
ችግር የለውም እያልክ ችግር አታከማች!
**ምንጭ፡-** የሕይወት ቀመሮች መጽሐፍ

## አለምን የቀየሩ ሳይንቲስቶች

የሰው ልጅ ዛሬ ለደረሰበት ዘመናዊ የአኗኗር ዘይቤ የብሩህ አዕምሮ ባለቤቶች የተለያዩ ሀሳቦችን አፍልቀዋል፣ ፍልስፍናቸውን አንፀባርቀዋል፣ እምነቶችን ፈጥረዋል፣ ምርምሮችን አድርገዋል፣ አስተምህሮቶችን ከጊዜ ወደ ጊዜ አሻሽለዋል። ቬሪያል ቶፕሊስት ኢሊትስ የተሰኘ የመረጃ ምንጭ አለምን የቀየሩ አስር ሳይንቲስቶችን ስም ዝርዝር አውጥቷል።

### 10. አርስቶትል (384 - 233 ዓመተ ዓለም)

ይህ ግሪካዊ ፈላስፋ በተለያዩ መስኮች አዳዲስ ሀሣቦችን አፍልቋል። እንስሳትንና እፅዋትን በባህሪያቸው በመመደብ ሌሎች ተከታዮቹ (ተተኪዎቹ) በጥልቀት እንዲያጠኑ በር ከፍቶላቸዋል።

### 9. አርኪመድስ (287 - 212 ዓመተ ዓለም)

ግሪካዊው አርኪመድስ ዛሬ የሰውን ልጅ ህይወት ያቀለሉትን የሒሳብና የፊዚክስ ትምህርት ቀመሮችን አበርክቷል። መላምትን ወደ ተግባር መለወጥ የጀመረ ሣይንቲስት ነው።

### 8. ጋሊሎ ጋሊሊ (1564 - 1642 ዓመተ ምህረት)

ጣሊያናዊው ጋሊሎ ጋሊሊ አባቱ ህክምና እንዲያጠና ወደ ኮሌጅ ቢልኩትም የእሱ ፍላጐት ወደ ሳይንስና ሒሣብ በማዘንበሉ የትምህርት መስኩን ቀየረ። የመጀመሪያውን ቴሌስኮፕ በመስራት ፕላኔቶችንና ከዋክብትን በሰራው መሣሪያ ለማየት በቃ። ለጠፈር ምርምሩ ጉልህ ድርሻ አበርክቶ አልፏል።

### 7. ሚካኤል ፋራዳይ (1791 - 1867 ዓመተ ምህረት)

በትውልድ እንግሊዛዊው ፋራዳይ ኤሌክትሪክን በመፍጠር አለምን ብርሐን አድርጓል

### 6. ቶማስ አልቫ ኤዲሰን (1847 - 1931 ዓመተ ምህረት)

ኤዲሰን በህይወት በቆየባቸው ዓመታት 1 ሺህ 93 ግኝቶችን ለአለም ለግሷል። አምፖል፣ ባትሪ፣ ቴሌግራፍ፣ የቁፋሮ ስራ፣ ሲሚንቶ ሐይል ወዘተ ግኝቶቹ መካከል ይጠቀሣሉ።

### 5. ሜሪ ሉዋንዶስኪ (1867 - 1934 ዓመተ ምህረት)

የምድራችን የመጀመሪያዋ ሴት ሣይንቲስት ሜሪ ሉዋንዶሲኪ የመጀመሪያውን ተንቀሣቃሽ ኤክስሬይ (Mobile X- ray) በመፍጠር ሴቶችን ወደ ሣይንስ የሣበች እንስት ነበረች።

### 4. ሊዊስ ፓስተር (1822 - 1895 ዓመተ ምህረት)

ሙሉ ህይወቱን በኬሚስትሪና በማይክሮ ባዮሎጂ ያሣለፈው ሊዊስ ፓስተር ነገሮችን ለማብላላት የሚያስችል ሣይንስን ፈጥሯል።

### ሰር አይዛክ ኒውተን (1643 - 1727 ዓመተ ምህረት)

የመሬት ስበት ህግን ለአለም አስተዋውቋል። ቁሳቁስን በቀላሉ ማንቀሣቀስ የሚችልበትንም ዘዴ አበርክቶ አልፏል።

### 2. አልበርት አንስታይን (1879 – 1955 ዓመተ ምህረት)

የክፍለ ዘመኑ ምርጥ ሰው አንስታይን የጠለቁ የፊዚክስ ቀመሮችን በማውጣት አለምን ወደፊት ያንደረደረ የዘላለም ሰው ነው።

### 1. ኒኮላ ቴስላ (1856 - 1943 ዓመተ ምህረት)

ይህ ባለብሩህ አዕምሮ በሣይንስ ቴክኖሎጂ ቁጥራቸው የበዙ ፈጠራዎችን አበርክቷል፡፡ ስምንት ቋንቋዎችን አቀላጥፎ መናገር ይችል የነበረው ኒኮላ ቴስላ ለዘመን ተጋረዎቹም ሆነ ከእሱ በኋላ ለመጡ እንደነ ኤዲሰን፣ ዋትሰን ዋት ማረኮኒና መሰል ሣይንቲስቶች ለፈጠራቸው ግኝቶች ተስላ ዋና መነሻቸው ነበር፡፡ "ተስላ ያልሰራው ስራ የለም" የሚል መለያንም አትርፎ አልፏል፡፡

/በወጋየሁ አንዳርጌ/
የካቲት 18/2008ዓ.ም

## የአባቴ ሦስቱ ምክሮች

የወቅቱ የቻይናው ፕሬዝዳንት ሺ ጂንግ ፒንግ ጥሩ ስትራቴጂ አዋቂና የሀገር መሪ ብቻ አይደሉም፡፡ ጥሩ ወግ አዋቂ ጭምር እንጂ፡፡ በአንድ ወቅት እንዲህ ሲሉ ስለልጅነት ጊዜያቸው ተናገረዋል፡፡

"ልጅ እያለሁ፣ እጅግ በጣም ራስ ወዳድና ሁሉንም ነገር ለኔ ባይ ነበርኩኝ" ይላሉ ፕሬዝዳንተ ሺ ጨዋታቸውን ሲጀምሩ፡፡ ለግማሽ ክፍለዘመን ወደኋላ በትዝታ እያሰቡ ፕሬዝዳንቱ ንግግራቸውን ቀጠሉ፡፡

ራስ ወዳድ ከመሆኔ የተነሳ ሁል ጊዜም ጥሩ ጥሩውን ለራሴ ነበር የምወስደው፡፡ ይህ ባህሪዬ ቀስ በቀስ ጓደኛ እያሳጣኝ መጣ፡፡ በመጨረሻም ጓደኞቼ ሁሉ ሸሽተውኝ ጓደኛ አልባ ሆንኩ፡፡ እኔ ግን ጥፋቴ ምን እንደሆነ አልገባኝም፡፡ ጓደኞቼ ስለሸሹኝ ኮነንኳቸው እንጂ ጥፋቴ ምን እንደሆነ ራሴን አልጠየኩም፡፡ ቢሆንም፣ አባቴ ሕይወትን በመልካም መንገድ እንዴት መምራት እንደምችል በተግባር አስተማረኝ፡፡

የአባቴ የሕይወት ትምህርት ሶስት ደረጃዎች ነበሩት፡፡ አንድ ቀን አባቴ፣ ለሁለታችን የሚሆን ምግብ አዘጋጀና በሁለት ሳህን ከፍሎ የምግብ ጠረጴዛ ላይ አስቀመጠው፡፡ ምግቡ ፓስታ (ኑድል) በእንቁላል ነበር፡፡ አባቴ ፓስታውን ሲያስቀምጠው በአንደኛው ሳህን ከፓስታው በተጨማሪ የተቀቀለ አንድ እንቁላል ከአናቱ አድርጎበታል፡፡ በሌላኛው ሳህን ግን ከፓስታው በላይ እንቁላል የለም፡፡ ከዚያ አባቴ ወደ እኔ እየተመለከተ፣ "ልጄ የትኛውን ትፈልጋለህ? አንዱን ሳህን ምረጥ" አለኝ፡፡

በጊዜው፣ እንቁላል እንዲህ በቀላሉ የሚገኝ ምግብ አይደለም፡፡ አዲስ ዓመት ካልመጣ ወይም ዓመትባል ካልደረሰ በቀር እንቁላል መብላት ዘበት ነው፡፡

ፈጥኜ እንቁላል ያለበትን ሳህን መረጥኩ፡፡ በሰዓቱ፣ ሳህኑን ሳነሳ ቅንጣት ታህል አላመነታሁም፡፡ ደስ እያለኝ መብላት ጀመርኩ፡፡

ፈጥኜ እንቁላል ያለበትን ሳህን መረጥኩ፡፡ በሰዓቱ፣ ሳህኑን ሳነሳ ቅንጣት ታህል አላመነታሁም፡፡ ደስ እያለኝ መብላት ጀመርኩ፡፡

አባቴ ሁለተኛውን ሳህን አንስቶ መመገብ ሲጀምር አይኔን አላመንኩም፡፡ አባቴ ከሚበላበት ሳህን ውስጥ ሁለት የተቀቀሉ እንቁላሎች በፓስታው ተሸፍነው ኖሯል፡፡ ተቆጨሁ በጣም! ቸኩዬ በመወሰኔ ራሴን ወቀስኩት፡፡

ይሄን ጊዜ አባቴ እየሳቀ፣ "የኔ ልጅ፣ አይኖችህ የሚያዩት ሁሉ እውነት እንዳልሆነ መቼም እንዳትረሳ! በሰዎች ላይ ብልጣብልጥ ለመሆን ስትሞክር ትጎዳለህ!!" አለኝ፡፡

በሌላ ቀን፣ አባቴ በተመሳሳይ ምግብ አዘጋጅቶ ሲያበቃ እንደተለመደው ፓስታውን በሁለት ሳህን አቀረበው፡፡ አንደኛው ሳህን አናት ላይ አንድ የተቀቀለ እንቁላል አስቀምጦበታል፡፡ በሌላኛው ግን ከላይ ምንም እንቁላል አላደረገበትም፡፡ ከዚያ እንደተለመደው አባቴ ወደ ምግብ ጠረጴዛው እየጠቆመ "ልጄ፣ ምረጥና የምትፈልገውን ሳህን ውሰድ" አለኝ፡፡

ካለፈው ስህተቴ በመማር በጥንቃቄ መምረጥ እንዳለብኝ አሰብኩና ቀልጠፍ ብዬ ከአናቱ እንቁላል የተደረገበትን ትቼ ሌላኛውን መረጥኩ፡፡ ከዚያ በፍጥነት ፓስታውን ገላለጥኩና ሳህኑን አየሁት፡፡ በጣም ደነገጥኩ! ሳህኑ ውስጥ አንድም እንቁላል የሚባል ነገር የለም፡፡

አባቴ በድጋሚ እየሳቀ፣ "ልጄ፣ ሁል ጊዜ በልምድህ ላይ ብቻ የምትተማመን ከሆነ ትከስራለህ፡፡ አንዳንዴ ሕይወት ራሷ ልታሞኝህ ወይም ቁማር ልትጫወትብህ ትችላለች፡፡ ዳሩ ግን፣ በዚህ ብዙ ልታዝን ወይም ልትቆጣ አይገባም፤ ትምህርት እንደሚሆንህ ቆጥረህ እለፈው፡፡ እንዲህ ያለውን እውቀት ከመማሪያ መፅሀፍት ላታገኝ እንደምትችል አስታውስ" ብሎኝ፣ ያ ቀን አለፈ፡፡

ለሶስተኛ ጊዜ አባቴ ምግብ አዘጋጀ፡፡ እንደተለመደው ፓስታ እና እንቁላል በሁለት ሳህኖች ቀርበዋል፡፡ በአንዱ ሳህን የተቀቀለው እንቁላል ከፓስታው በላይ ተቀምጧል፡፡ በሌላኛው ሳህን ደግሞ ፓስታ ብቻ…፡፡ የውስጡን አላውቅም፣ ከላይ ግን እንቁላል የለም፡፡ አባቴ የተለመደው ጥያቄውን አቀረበልኝ፡፡ ወደ ምግብ ጠረጴዛው እየጠቆመ፣ "ልጄ ምረጥ! የትኛው ሳህን ይሁንልህ?"

አሁን እኔ ከሁለት ሥህተቶቼ ትምህርት አግኝቻለሁ፡፡ "አባቴ አንተ የቤቱ አባወራ ነህ! ለቤተሰባችን ሰርክ የምትለፋ አባት ነህ፡፡ መጀመሪያ መብላት ያለብህ አንተ ነህ፤ ይገባሃልም፡፡ ስለዚህ ቅድሚያ አንተ አንሳ…" ስል መለስኩለት፡፡

አባቴ በጭራሽ አላቅማማም…፡፡ ከአናቱ እንቁላል የተቀመጠበትን ሳህን አንስቶ መብላት ጀመረ፡፡ እኔም ሁለተኛውን አንስቼ ፓስታዬን ለመብላት አቀረቀርኩ፡፡ እርግጠኛ ነበርኩ፣ ሳህኑ ውስጥ እንቁላል እንደማይኖር፡፡ ከፓስታው በታች ሁለት እንቁላሎችን ሳገኝ ግን አይኔን ማመን አልቻልኩም፡፡

ቀና ብዬ ሳየው፣ አባቴ ፈገግ ብሎ በፍቅር አይኑ እያስተዋለኝ ነበር፡፡ ከዚያም እንዲህ ሲል መከረኝ፤ "የኔ ውድ ልጅ! ለሌሎች ሰዎች መልካም መልካሙን ስታደርግ ተፈጥሮ ራሷ መልካም መልካሙን ወደ አንተ ታመጣለች! ይሄንን መቼም እንዳትዘነጋ" አለኝ፡፡

ከዚያን ጊዜ በፊትም ሆነ፣ ከዚያን ጊዜ በኋላ አባቴ ብዙ ጊዜ መክሮኛል… ገስፆኛል፡፡ አብዛኞቹን ማስታወሴን እጠራጠራለሁ፡፡ ነገር ግን፣ እነዚህ ሦስት ምክሮቹን በፍፁም አልረሳቸውም… እስክሞት ድረስ፡፡ እነሆ ሕይወቴም በዚህ ምክንያት የተስተካከለ ሆኗል፡፡ ከአባቴ ምክር በኋላ ስኬት መንገዷን ወደ እኔ አድርጋለች፡፡

# አቅም

## ኢንተርፕረነርሽፕ ልማት ምንነት፣ ሀገራዊ ፋይዳና ተሞክሮ

### በተቋሙ የኢንተርፕረነርሽፕ ልማት ዳይሬክቶሬት

በተቋሙ የኢንተርፕረነርሽፕ ልማት ዳይሬክቶሬት

ሃገራዊ የኢኮኖሚያዊ መዋቅራዊ ለውጥ ለማምጣት ስር ነቀል የኢኮኖሚ ሽግግር ማምጣት አስፈላጊ በመሆኑ የኢትዮጵያ ኢንተርፕራይዝ ልማት በአዲስ መልክ ተቋቁሟል። ይህን ተከትሎ በየደረጃው መዋቅሩን በመዘርጋት ውጤታማ ድጋፍ ለማድረግ ጥረት እየተደረገ ይገኛል። የኢንተርፕረነርሺፕ ልማት ስራውን ለማሳለጥም በፌዴራል ደረጃ ትኩረት ተሠጥቶበት እየተሠራበት ይገኛል።

ተቋሙ በኢንተርፕሩነር ዙርያ አመራሮችን፣ ባለሙያዎችን፣ ኢንተርፕረነሮችን የአቅም ክፍተት በመለየት ስልጠና እንዲያገኙ ማድረግ፣ የምክርና ንግድ ልማት አገልግሎት በመስጠት ሥራ ፈጠራን እና የኢንተርፕራይዞችን ተወዳዳሪነት የማጎልበት ተግባርና ሃላፊነት አለው።

በዚህ መሠረት በአምራች ዘርፍ በየአደረጃጀቱ ያሉ የፈጠራ ባለቤቶችን፣ ሥራ ፈጣሪ ባለሃብቶችን፣ የፈጠራ ሃሳብና ወይም ሃብት ያላቸው ጀማሪ ኢንተርፕረነሮችን በመለየት እና ወደሥራ እንዲገቡ ለማድረግ የሚያስችሉ የአሠራር ድጋፎችን፣ ልምዶችንና ተሞክሮዎችን እንዲቀስሙ የማነሳሳትና የማነቃቃት ሥራ ጭምር በመስራት ላይ ይገኛል።

ለዜጎች ሥራ ዕድል ከመፍጠር፣ የግል ገቢን ከማሳደግ እና ትርፍ ከማግኘት ባሻገር ሳይንሳዊ እና ዓለም አቀፋዊ ይዘት ያለው የንግድ ሥራ ጀግና (business hero) የመሆን ራዕይ አንግበው የሚንቀሳቀሱ ሥራ ፈጣሪዎችን ለመፍጠር የሚያስችል ምቹ ሁኔታ መፍጠር ያስፈልጋል።

ስለዚህ እንደተቋም በሃገር ውስጥና በውጭ ሃገር ከሚገኙ ባለድርሻ አካላት ጋር በመቀናጀት የኢንተርፕረነርሺፕ ልማትን ለማስፋት ከምንሰራቸው ሥራዎች አንዱ የሆነው የኢንተርረነርሺፕ ልማት የአቅም ግንባታ ሥልጠና ነዉ።

ተቋሙ ኢንተርፕራይዝ ተኮር በሆነው የኢንተርፕሩነርሽፕ ድጋፉ ፣ የቢዝነስ ዕቅድ (business plan) ዝግጅት፣ የንግድ ምክርና የንግድ ልማት አገልግሎት (Business Development Service) ላይ በየደረጃው የሚገኙ አመራሮችንና ባለሙያዎችን የኢንተርፕረነርሺፕ ልማት አቅም ግንባታ የአሰልጣኞች ሥልጠና መስጠት፣ በተዋረድ የፈጠራ ባለቤቶችን፣ ሥራ ፈጣሪ ባለሃብቶችን፣ የፈጠራ ሃሳብ ባለቤቶችን፣ ጀማሪ ኢንተርፕረነሮችን በመለየትና ያሉባቸውን የአመለካካት ክፍተት ለመቅረፍ የሚያስችሉ በፍላጎት ላይ የተመሠረቱ የኢንተርፕረነሮች መርሃ ግብር መቅረጽ፣ የኢንተርፕረነሮች ተሞክሮ መቀመርና ማስፋት፣ ሃገር አቀፍና ዓለም አቀፍ ተቋማትን ለጋራ ዓላማ ማቀናጀትና ማስተባበር ዋና ዋናዎቹ ናቸው።

በመሆኑም የአምራች ኢንዱስትሪ ባለቤቶችና ሠራተኞች፣ የወጣትና የሴት አደረጃጀቶች የቴ/ሙ/ት/ሥልጠና እና የዩንቨርሲቲ ምሩቃን፣ አርሶና አርብቶ አደሮች፣ የንግድና የአገልግሎት ዘርፍ ባለሃብቶች አደረጃጀቶች የኢንተርፕረነርሽፕ አመለካከት ለውጥ ንቅናቄ መፍጠር የግድ ይላል።



በአጠቃላይ በየደረጃው በሦስቱም የልማት ኃይሎች የሚታዩትን የሥራ ፈጣሪነት አስተሳሰብና ቁርጠኝነት ክፍተቶች በጥናት ለይቶ በተከታታይ በኢንተርፕሪነርሽፕ የአቅም ግንባታ ስልጠና ሂደት መፍታት አስፈላጊ በመሆኑ እና ኢንተርፕራይዞችና ሌሎች ወደ ዘርፉ የሚገቡ ዜጎችን በዓለም አቀፍና በሃገር ውስጥ ገበያ ተወዳዳሪ እንዲሆኑ ከሚሰጡት የቴክኒክና የፋይናንስ ድጋፎች ባሻገር በኢንተርፕረነርሽፕ አመለካከትና ክህሎት ማነቆዎች ምክንያት አምራች ዘርፉ እየገጠመው ያለውን ችግር ለመቅረፍ የኢንተርፕረነርሽፕ ልማት አቅም ግንባታ መመሪያ ተዘጋጅቷል።

መመሪያው በተለይ በወጣት፣ በሴቶች፣ እንዲሁም የአካል ጉዳተኞችን ተሳትፎና ተጠቃሚነት በሚያረጋግጥ መልኩ የተቀረጸ ነው።

በተለይ የአመለካካት ቀረጻ ተጨባጭ ለውጥ እንዲያመጣ የኢንተርፕረነርሺፕ ልማት ከመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት ጀምሮ የትምህርት ሥርዓታችን ላይ ያልተካተተ በመሆኑ የነገ ሃገር ተረካቢ ታዳጊዎችና ወጣቶች ስለ ሥራ ፈጠራ ጥበብ ያላቸው አስተሳሰብ እጅግ የወረደ እና በአመዛኙ ጊዜያቸውን በባልተገባ ቦታ የሚያሳልፉ መሆናቸው አንድ ማሳያ ነው።

በሃገራችን ኢንተርፕረነሮችን ለማበረታት የሚያስችል የተቀናጀ አቅም ያለው ጠንካራ አደረጃጃት አለመኖር፣ የከፍተኛ የትምህርት ተቋማት፣ የዘርፍ ማህበራት፣ ዓለም አቀፍ ተቋማት፣ የኢንዱስትሪ ልማት ተቋማት፣ የጥናትና ምርምር ተቋማት እና፣ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን ያሳተፈ፣ ዘላቂነት ያለው ቅንጅታዊ አሠራር ያልተዘረጋለት በመሆኑና፣ በትምህርት ሥርአት ውስጥ በተገቢው ያልተካተተ ወይም የሥልጠና አሰጣጥ ስርዓቱ ለዋጭ ባለመሆኑ የሚፈለገውን ያህል ለኢንዱስትሪ የሚሆን የሰው ሃይል ማፍራት ላይ ሰፊ ውስንነት እንዳለዉ በተደጋጋሚ ከኢንተርፕራይዝ ባለቤቶች ጋር በሚደረጉ የክትትልና የድጋፍ ስራዎች ወቅት የሚነሱ ጉዳዮች ናቸው።

በኢንተርፕራይዝ ልማት ዘርፍ የሚገኙ አመራሮችና ባለሙያዎች፣ በኢንተርፕረነሮች፣ በወጣቶች፣ በሴቶችና ሌሎች የህብረተሰብ ክፍሎች ላይ የሥራ አመራር፣ የፋይናንስ አጠቃቀም፣ የአሰራርና አደረጃጀት፣ የአካባቢን ፀጋ አሟጦ የመጠቀም፣ ዘርፉ ከግል ጥቅም ባሻገር ዘላቂ ሃገራዊ ራዕይ ሰንቆ ያለመሄድ፣ የእሴት ሰንሰለትን ሂደትን ተከትሎ የአምራች ኢንዱስትሪ ማስፋፋት ሃገራዊ ተወዳዳሪነት፣ ሰፊና ዘላቂ የሥራ ዕድል የሚፈጥር መሆኑን ያለመረዳት እንዲሁም ዘመናዊ የሆኑ ቴክኖሎጂዎችን በመጠቀም ጥራት ያለውና ተወዳዳሪ የሆነ ምርት ማምረት እንደሚችሉ ያለማወቅና የመሳሰሉት ችግሮች ይገኙበታል።




በመሆኑም ይህንን ችግር ለመፍታት በሀገሪቱ ባሉ ዩኒቨርስቲዎች፣ በቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ኮሌጆች እና ሌሎች መንግስታዊና መንግስታዊ ባልሆኑ ተቋማት ሥር የሚገኙ የኢንተርፕረነርሽፕ ልማት አደረጃጀቶች የሚያጠናክርና አዳዲሶችንም እንዲቋቋሙ የሚያስችል የአሰራር ሥርዓት በመዘርጋት በገጠርም ሆነ በከተማ ያለውን የሥራ ፈጠራ ጥበብ ተነሳሽትና ባህልን በማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ዘርፉ ላይ ማሳደግ ያስፈልጋል።

በኢንተርፕሩነርሽፕ ዙርያ መጠነኛ ግንዛቤን ለመያዝ እንዲቻል በሳይንሱ ዙርያ ያሉ ዋና ዋና ጉዳዮችን ቀለል ባለ መንገድ ከዚህ በታች ለማስተዋወቅ ይሞክራል።

## የሥራ ፈጠራ ጥበብ (ኢንተርፕሪነርሽፕ) ማለት ምን ማለት ነው?

ቃሉ አንድ ወጥ የሆነ ዓለም አቀፍ ትርጉም የለዉም። የዘርፉ ምሁራን የተለያዩ ፍችዎችን ሰጥተዉታል። "ኢንተርፕሪነርሽፕ" የሚለዉ ቃል (ኢንተርፕራንደር) ከሚለዉ የፈረንሳኛ ቃል የተወሰደ ነዉ።

ይህም ማለት ኃላፊነት መዉሰድ (risk taking) አንድን ነገር ከሌላዉ በተለየ መንገድ መስራት (ማድረግ) ብለዉ ይተረጉሙታል። ሌሎች የሚፈሩትን ኃላፊነት ወስዶ መስራት እንደማለት ነዉ።

**ኢንተርፕሪነርሽፕ፡-** ቋሚና ፈጣን የሆነ አዳዲስ ተጨማሪ ኃብት የመፍጠር ሒደት ወይም ችሎታ ነዉ። ኢንተርፕሪነርሽፕ ሂደት ነዉ። አንዴ ተሰርቶ የማያልቅ እና ቀጣይነት ያለዉ ሂደት ነዉ።ይህም እንቅስቃሴ አዳዲስ ምርቶችንና አገልግሎቶችን ቢዝነስ (የንግድ ሥራ) ከመፍጠር ጋር ይያያዛል።

ጆሴፍ ሹምፕተር የተባሉ ኦስትሪያዊ አሜሪካዊ "ኢንተርፕሪነርሽፕ" ነባር አሰራሮችን በአዲስና በተሻሉ ዘዴዎች የመተካት ሂደት ነዉ ይላሉ።

ሁልጊዜም አንድን ስራ ለመስራት የሚያስችሉ የተሻሉ ዘዴዎችን መፍጠር ይቻላል ብሎ የሚያስብና የሚተገብር ነዉ።

**ኢንተርፕሪነርሽፕ** ማለት በህይወታችን የተለያዩ ምቹ አጋጣሚዎችን በመጠቀም አዳዲስ ነገሮችን ፈጥሮና አክሎ በመስራትና አንድን ምርት በአዲስ መልክ አሻሽሎ በማቅረብ በአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ በማለፍ በኑሮ ላይ ለውጥ/ዕድገት የማምጣት ሂደት ነው።

## የሥራ ፈጠራ (ኢንተርፕሪነርሽፕ) ልማት ጠቀሜታ

- በአካባቢ የሚገኙ ጸጋዎችን (ሃብቶችን) እሴት በመጨመር ገበያ ላይ የሚኖራቸውን ዋጋ ከፍ እንዲል ያደርጋል፤
- ነባር እና አዳዲስ የቴክኖሎጂ ፈጠራዎችን እና የስራ ፈጠራ ባህልን ያዳብራል፤
- ጤናማ ሃብት በማፍራት ሃገራዊ እና ዓለም ዓቀፋዊ የምጣኔ ሃብት ልማት ግቦችን ለማሳካት ያግዛል ፣
- ሃገር አቀፍና ዓለም ዓቀፍ ተወዳዳሪነትን ለማሳደግ፣
- ለስራ ዕድል ፈጠራ፣ የዜጎችንና የሃገር ምርታማነትን ለማሳደግ፣

## የኢንተርፕሪነርሽፕ (የስራ ፈጠራ ጥበብ) ሂደት ዉህደቶች ምንድን ናቸዉ?

- ራዕይ መኖር፤
- የዉስጥ የሥራ ተነሳሽነት መኖር፤
- የአካባቢ ጸጋን እና ሁኔታን መቃኘት፤
- ምቹ የስራ ዕድሎችን (አጋጣሚዎችን) መለየትና መምረጥ፣
- ለስራው አስፈላጊ የሆኑ ግብአቶችን ማሰባሰብና ወደ ትግበራ መግባት፤
- በመስራት ኃብት ማፍራት እንደሚቻል የሚያምን እና የተገኘውን ውጤት በአግባቡ መጠቀም የሚችል፤
- ሐላፊነትን መሸከም እና መወሰን ብሎም እርምጃ መዉሰድ መቻል፤
- ለዉጥን የመሻት፣ ፈጥኖ ለለዉጥ ምላሽ የመስጠት፣ የመጠቀም ችሎታ፤ወዘተ ናቸው

## ኢንተርፕሪነር(ስራ ፈጣሪ) ምን ማለት ነው?

ኢንተርፕርነር ማለት በራሱ ተነሳሽነት ያሉትን የንግድ ስራ አጋጣሚዎችን በመፈተሽና በመለየት በአካባቢ ያሉ ሃብቶችን በአግባቡ በመጠቀም በውጤት ላይ ያተኮረ ስራ ላይ የተሰማራ እና ሊመጡ የሚችሉ ችግሮችን ከወዲሁ በመገመት አስፈላጊውን ጥንቃቄ የሚያደርግና የተሰላ ሃላፊነት (calculated risk) መውሰድ የሚችል የንግድ ሰው ነው።

**ኢንተርፕሪነር** (ስራ ፈጣሪ) እና በፈጠረዉ ስራ ከራሱ አልፎ ሌሎችን መቅጠር የሚችል ነዉ። የጀመረዉን የንግድ ስራ ወደ ተሻለ ደረጃ የሚያሸጋግር እና በዚህ የሽግግር እንቅስቃሴዉ ሁሉ ተጨማሪ የስራ እድሎችን የሚፈጥር፤አዲስ ምርትንና ሃብትን መፍጠር የሚያስችሉ እንቅስቃሴዎች ላይ የሚያተኩር የንግድ ሰዉ ነዉ ።

## ኢንተርፕሪነር(ስራ ፈጣሪ) ምን ማለት ነው?

- ራዕይ ያለዉ የተጠና ንግድ ስራ ላይ ጊዜዉን፣ ገንዘቡንና ዕዉቀቱን የሚያዉል እና በእቅድ የሚመራ ያቀደዉን ራዕይና አላማ እዉን ለማድረግ የሚያስችል የፈፃሚነት ኃይልና ብቃት ያለዉ ነዉ።
- ለሚሰሩ ስራዎች የተሻሉ መንገዶች አሉ ብሎ የሚያምንና የሚሰራ እና ለዘመናዊ የንግድ ስራ ዘርፎች ላይ አብዛኛዉን ጉልበቱን፤እዉቀቱንና ጊዜዉን የሚያዉል ነዉ።
- ኢንተርፕረነር ህብረተሰቡን የሚያነቃንቅና በሚፈጥራቸዉ አዳዲስ ነገሮች ህብረተሰቡን የሚያንቀሳቅስ ነዉ (Entrepreneurs are movers and shakers of the society)

በአጠቃላይ ኢንተርፕረነሮች በማህበራዊ፤ በኢኮኖሚያዊ፤ በፖለቲካዊ የሀገር እንቅስቃሴዎች ዉስጥ ጉልህ ለዉጥ የሚያመጡ ሥራ ፈጣሪዎች ናቸዉ።

➤ **የፈጠራ ችሎታ / Creativity እና ፈጠራ /ግኝት / Innovation**

**የፈጠራ ችሎታ:-** ከዚህ በፊት ያልነበረ አዲስ ነገርን የማምጣት ችሎታ ነው።

ይህ ትርጓሜ የሚያተኩረው ተግባር ላይ ሳይሆን አዲስ ነገር የመፍጠር ችሎታ( ability) ላይ ነው።

ስለዚህ አንድ ሰው ስለአዲስ ነገር ሲያስብ እና እንዴት ይህን ነገር መጠቀም እንደሚቻል ማሰብን ይጨምራል ።

➤ የፈጠራ ችሎታ አንድን ነገር በአዲስ ወይም በተለየ መንገድ የመስራት ወይም የመንደፍ፣የመቅረጽ ችሎታ ነው።

➤ የፈጠራ ችሎታ ለችግሮች/ፍላጎቶች መፍትሄ ሊሆን የሚችል ኢኖቬቲቭ ሃሳቦችን የማምጣት እና ገበያ ላይ የማዋል አቅም ነው። አንድ ሥራን የመፍጠር ችሎታ ዘወትር በንግድ ሥራ ውስጥ ስኬታማ የመሆን ወይም ያለመሆን ልዩነት ነው።

➤ የፈጠራ ችሎታ ብዙውን ጊዜ ከተለመደው ወይምፈጣን እድገት ወይም ዳይናሚክ የንግድ ሥራዎች ይለያል።

➤ ሥራ ፈጣሪ ለመሆን ሥራ ፈጣሪዎች ጭንቅላታቸውን እና ዓይናቸውን ለአካባቢያቸው ክፍት ማድረግ ያስፈልጋቸዋል።

➤ **ፈጠራ /ግኝት / Innovation**

ኢኖቬሽን አዲስ ነገሮችን ወደ ሥራ የመቀየር ሂድት ነው። አዲስ ሃሳቦች ወደ ምርት፣ አገልግሎትና አሰራር እስከሚቀየሩ ድረስ ብዙም ዋጋ አይኖራቸውም።

ስለዚህ ኢኖቬሽን ማለት አዲስ የመነጩ ሃሳቦችን ወደ ጠቃሚ ነገሮች መለወጥ ሲሆን የፈጠራ ችሎታ ግን የኢኖቬሽን ቅድመ ሁኔታ ነው።

የፈጠራ ችሎታ ለሥራ ፈጣሪነት የሚያነሳሳ መነሻ (ዘር) ከሆነ ኢኖቬሽን ደግሞ ለሥራ ፈጣሪነት ሂደት ነው።



እንስቷ

## ከነዓን ጋርመንት፣

# ራስ ተነሳሽነትና የመንግስት ድጋፍ ውብ ጥምረት ማሳያ!

በሮቤል አህመድ

ፈጣሪ የሰውን ልጅ ሲፈጥረው ከሌሎች በተለየ መልኩ ብልህና የተሻለ አድርጎ ነው፡፡ ስኬት ላይ ለመድረስም በርትቶ የሚሰራ ከሆነ ውጤታማ መሆን ይችላል፡፡ ውጤትና ስኬት ላይ ለመድረስ ደግሞ ጠንክሮ መማር ይጠይቃል፡፡ ህልም ካለና ተግቶ መስራት የቤተሰብ እገዛ የሚጨመርበት ከሆነ በአጭር ግዜ ውስጥ ያሰቡበት ቦታ መድረስ ይቻላል፡፡ ለዚህ ማሳያ የሚሆነን የዛሬዋ ባለታሪካችን የህይወትና የስራ ተሞክሮ ሲሆን ባለታሪካችን ሳሮን ጌታቸው ትባላለች፡፡

እድሜዋ በሃያዎቹ መጨረሻ አካባቢ የሚገኝ ወጣት ናት፡፡

ትውልዷ ነቀምት ሲሆን ትምህርቷን የተከታተለችው አዲስ አበባ ከተማ ነው፡፡ የመሰናዶ ትምህርቷን አዲስ አበባ ካጠናቀቀች ኋላ ከባህር ዳር ዩኒቨርስቲ በጋርመንት ኢንጂነሪንግ የመጀመሪያ ዲግሪ ትምህርቷን በ2008 ዓ.ም ጨርሳለች፡፡

ከዩኒቨርስቲ እንደተመረቀች እንደሌሎች ወጣቶች ተቀጥራ ለመስራት የማስታወቂያ ሰሌዳን ማማተር አላሻትም፤ ይልቁንስ በዩኒቨርስቲ ቆይታ ያገኘችውን እውቀት በመጠቀም ከጓደኞችዋ ጋር በመሆን በማህበር በመደራጀት ከግዜ በኋላም የራሷን ድርጅት በመክፈት ከራሷ አልፋ ለበርካታ ወጣቶች የስራ እድል ፈጥራለች፡፡

የዝግጅት ክፍላችንም የዚችን ወጣት ስራ ፈጣሪ ልምድና ተሞክሮ ሊያስቃኛችሁ መዳረሻውን ከአዲስ አበባ በስተምስራቅ 74 ኪ/ሜ በምትርቀውና የበርካታ ኢንዱስትሪዎች መገኛ በሆነችው ሞጆ ከተማ አድርጓል፤ እንድትከታተሉን ጋበዝናችሁ፡፡

ወጣት ሳሮን ጌታቸው በባህር ዳር ዩኒቨርስቲ የጋርመንት ኢንጂነሪንግ ተማሪ በነበረችበት ወቅት መንግስት ለጨርቃ ጨርቅ ዘርፍ ከፍተኛ ትኩረት መስጠት የጀመረበት ወቅት እንደ ነበር ትናገራለች፡፡

ከዚህም ባለፈ የኢንዱስትሪ ፓርኮች በተለያዩ ከተሞች መከፈት የጀመሩበት ወቅት ነበር፡፡

የዩኒቨርስቲ መምህራኖቿም ተቀጥሮ ከመስራት ይልቅ ስራ ፈጣሪ መሆን አዋጭ እንደሆነ ሁሌም ይነግሯት ስለነበር ይህ ጉዳይ ትኩረቷን እንደሳበው ትናራለች፡፡

በጋርመንት ዘርፍ ብትሰማራ ከራሷም አልፋ ለሌሎች ሰዎች ስራ መፍጠር እንደምትችል እምነት ስለነበራት ዘርፉን ተቀላቅላለች፡፡

ቤተሰቦቻቸው ለምርቃት የሰጧቸውን ስጦታ እንደመነሻ በማድረግ ከዩኒቨርስቲ ጓደኞቿ ጋር በጋርመንት ሙያ ተሰማርተው መስራት የጀመሩት፡፡



ለምርቃት የተሰጣትን ስጦታ እንደሌሎች ተመራቂ ተማሪዎች ለአልባሌ ነገርና ለጊዚያዊ ነገር ከማዋል ይልቅ ለስራ የሚያገለግላትን ማሽን ለመግዛት ተጠቀመችበት፡፡

ሳሮን ይህን ስታስታውሰው እንደምትደሰትና ይህ ስራ ለሌሎች ወጣቶች አርአያ እንደሚሆን ትገልጻለች፡

፡ ከዩኒቨርስቲ ተመርቃ እንደ መጣች መንግስት ባመቻቸላት እድል መሰረት ለ2 ወራት የቆየ ስልጠናና ተሞክሮ ወሰደች፡፡

ይህም ልብስ ስፌት ላይ የተሻለ እውቀት እንዲኖራት እንዳስቻላት የምትገልጸው ሳሮን ከስልጠናው በተጨማሪ በመንግስት ለዘርፉ የተመቻቹ እድሎችን በተመለከተ ግንዛቤ ማግኘቷን ታስታውሳለች፤ ይህም ነገሮችን ቀላል እንዳደረገላት ትገልጻለች፡፡

ሳሮንና ጎደኞቿ ከቤተሰብ የተሰጣቸውን ስጦታ እንደመነሻ በማድረግ ከኢትዮጵያ ልማት ባንክ የተለያዩ ማሽኖች በብድር ካገኙ በኋላ ወደ ስራ ገብተዋል፡፡

ስራም እንደጀመሩ ውጤታማ በመሆናቸው በብድር ያገኙትን ማሽኖች ከፍለው ብድራቸውን መለሱ፡፡

ሳሮን ዘርፉ ውጤታማ መሆኑን ከተረዳችና ከጓደኞቿ ጋር ለጥቂት ዓመታት ከሰራች በኋላ ከትዳር አጋሯ ጋር በመሆን የራሷን ድርጅት ከነአን ጋርመንት በሚል ስያሜ በ2012 ዓ.ም በ500 ሺህ ብር ካፒታል ስራ ጀመረች፡፡

የትኛውንም ዓይነት የጋርመንት ስራ እንደምትሰራ የምትገልጸው ሳሮን ከተለያዩ ድርጅቶች የሚሰጣቸውን የስፌት ትዕዛዞች በብዛት በመስፋት በአጭር ግዜ ማስረከብ የሚችሉበት አቅም ላይ እንደደረሱም ትናገራለች፡፡ ከዚህም ባሻገር ጥናትን መሰረት በማድረግ የተለያዩ ልብሶችን በመስፋት ለገበያ ያቀርባሉ፡፡

ለውጭ ሀገራት የሚላኩ ምርቶችንም እንዲሰፉ በተጠየቁበት ወቅት በጥራት በማምረት ማስረከባቸውን ታስታውሳለች፡፡

የስፌት ስራዎች የሆኑትን እንደ ሸሚዝ፣ ጂንስ ሱሪ፣ የደንብ ልብሶች፣ ዩኒፎርሞች፣ የህጻናት ልብሶችና ሌሎች አልባሳትን በመስፋት ለገበያ ያቀርባሉ፡፡

የጋርመንት ዘርፍ እንደኢትዮጵያ ላሉና በርካታ የህዝብ ቁጥርና የስራ አጥ ቁጥር ላላቸው ሀገራት የስራ አጥን ቁጥር ለመቀነስ ወሳኝ መሆኑን የምትገልጸው ሳሮን በአሁኑ ሰዓት በድርጅቷ ውስጥ 200 ለሚሆኑ ወጣት ሴቶች በአጠቃላይ 238 ለሚሆኑ ዜጎች የስራ እድል መፍጠሯን ትናገራለች፡፡

‹‹አሁን ለደረስኩበት ደረጃ በቀላሉ ያለምንም ተግዳሮት እዚህ የደረስኩ ይመስላቸዋል›› የምትለው ሳሮን እዚህ ደረጃ ለመድረስ በርካታ ችግሮችን፣ ውጣ ውረዶችንና መመላለሶችን በጽናት በማለፍ መሆኑን በኩራት ታስታውሳለች፡፡

ስራውን እንደ ጀመረች አካባቢ የካፒታል እጥረት ትልቁ ተግዳሮት እንደ ነበር የምትገልጸው ሳሮን የጥሬ እቃ አቅርቦትም አስቸጋሪ እንደነበር ትናግራለች፡፡

በተለይም ገበያ ለማግኘትና ከሰው ጋር ለመተዋወቅ እንደተቸገረችና በርካታ ስራ እንደጠየቃት ትገልጻለች፡፡

“ስራው ላይ በሚፈለገው ደረጃ ለመግባት ድጋፍ የሚሰጥና ትስስር የሚፈጥር ሰው ማግኘት ከባድ ነበር” የምትለው ሳሮን በተለይም የስራ መጀመሪያ ግዜያት እገዛ የሚያስፈልግበት ወቅት ነው ትላለች፡፡

‹‹ትክክለኛውን መንገድ የሚያሳየን አካል አልነበረም!›› የምትለው ሳሮን ሁሉንም በሮች በራሳቸው ጥረት በማንኳኳት ወደ ስራው እንደ ገቡ ታስታውሳለች፡፡

‹‹አንዳንድ ግዜ ያደረግናቸው ጥረቶች ሳይሳኩ ሲቀር ወደኋላ ያልንበት ግዜ ቢኖርም ራዕይ ስለነበረን ችግሮችን በትግስትና በብልሃት በመጋፈጥ እዚህ ደረጃ መድረስ ችለናል›› ትላለች፡፡

አምራቹንና ገበያውን የሚያስተሳስርና የሚያገናኝ አካል አለመኖሩ ስራውን ከባድ አድርጓባቸው እንደነበር የምትገልጸው ሳሮን በአስፈጻሚ አካላት በኩል የነበረው ቢሮክራሲና መጓተቶች ፈተና እንደነበሩ ትገልጻለች፡፡

ይህን ሁሉ በማለፍ አሁን የደረሰችበት ሁኔታ ለራሷ ጥንካሬ እንደሆናት በኩራት ትገልጻለች፡፡

በመንግስት አካላት በርካታ ድጋፎች እንደተደረገላት የምትገልጸው ሳሮን የመንግስት ድጋፍ እዚህ ለደረሰችበት ደረጃ መድረስ ትልቅ አስተዋጽ እንዳለው ትገልጻለች፡፡

የተለያዩ ስልጠናዎችን በሀገር ውስጥም ሆነ በውጭ ሀገር እንደወሰደች የምትገልጸው ሳሮን ይህም ለስራዋ ውጤታማነት ትልቅ አስተዋጽኦ እንዳለው ትናገራለች፡፡

በስልጠና ሂደትም የጋርመንት ዘርፍ አዋጭነት እንዲሁም ለስራ እድል ፈጠራው ያለውን አስተዋጽኦ መረዳቷንና ውስጧ ያለውን አቅም እንድታወጣና እንድትጠቀም ትልቅ አቅም እንደፈጠረላት ትናገራለች፡፡



በተጨማሪም ለጋርመንቱም ሆነ ለሰራተኛ ምቹ የሆነ 3 ሺህ 5 መቶ ካሬ የሚሆን የማምረቻ ሼድ በኪራይ እንድናገኝ መደረጉ ትልቅ እገዛ ነው የምትለው ሳሮን በተጨማሪም ማሽነሪዎችን ከቀረጥ ነጻ ከውጭ እንድታስገባ መደረጉ ትልቅ እገዛ መሆኑንና ለስራው ስኬት አስተዋጽኦ ማድረጉን ትገልጻለች።

ከተለያዩ የኒቨርስቲዎችና ቴክኒክና ሙያ ኮሌጆች በዘርፉ የሰለጠነ የሰው ሃይል እንድታገኝ መንግስት ከጎኗ በመሆኑ ለዘርፉ ስኬት ትልቅ አስተዋጽኦ መሆኑን ትናገራለች።

በተጨማሪም ከትላልቅ ካምፓኒዎች ግብዓቶችን እንድታገኝ ድጋፍ እየተደረገላት እንደሆነ የምትገልጸው ሳሮን በዘርፉ ያሉ መረጃዎችን በተመለከተ የማማከርና የማገዝ ስራ በመንግስት በኩል እየተደረገላት በመሆኑ ደስተኛ መሆኗን ትገልጻለች።

በአሁኑ ሰዓት በየትኛውም ደረጃ የሚገኙ የመንግስት አስፈጻሚ አካላት በር ክፍት እንደሆነና የምትፈልገውን እገዛ እንደምታገኝ የምትገልጸው ሳሮን ይህም መንግስት ለዘርፉ የሰጠውን ከፍተኛ ትኩረት ማሳያ መሆኑን ትገልጻለች።

ስራዋን በ500 ሺህ ብር መነሻ ካፒታል የጀመረችው ሳሮን በሁለት ዓመት ግዜ ውስጥ ካፒታሏን 8 ሚሊዮን ብር ማድረስ ችላለች።

ስራዋን ስትጀምር 60 የሚሆኑ ሰራተኞችን ይዛ የጀመረች ሲሆን በአሁኑ ሰዓት 238 የሚሆኑ ሰራተኞችን ቀጥራ በማሰራት ላይ ትገኛለች። ከእነዚህም ውስጥ 200 የሚሆኑት ሰራኞች ሴቶች ናቸው።

አብዛሃኛዎቹ ሰራተኞች ሲቀጠሩ ልምድ እንዳልነበራቸው የምትገልጸው ሳሮን ሰራተኞቹ ስራ ሲጀምሩ የተሟላ ስልጠና ተሰጥቷቸው ወደስራ እንደሚገቡና በዚህም ሰራተኞቹም ሆነ እርሷ ደስተኛ መሆኗን ትገልጻለች።

የክፍያ ስርዓቱን በተመለከተ ስራንና ትርፍን መሰረት ያደረገ ሲሆን እያንዳንዱ ሰራተኛ የሚከፈለው በሰራው ስራ ልክ ማበረታቻ እየተሰጠው ሲሆን ድርጅቱ ከሚያገኘው ትርፍ ሁሉም ሰራተኛ በሰራው ስራ ልክ የሚያገኝ ይሆናል።

ይህም ሁሉም ሰራተኛ በባለቤትነት ስሜት እንዲሰራ የሚያግዝ ሲሆን በዚህም ሁሉም ሰራተኞች ደስተኞች ናቸው።

ስራዋን ዘመናዊ ለማድረግ በተቻለ አቅም ትስስሮችን እየፈጠሩ እንደሆነ የምትገልጸው ሳሮን በዘርፉ የተሻለ ስራ ከሰሩ ሰዎች ተሞክሮ በመውሰድ እንዲሁም ከሲሪላካና ቻይና ዜጎች ልምድ በመውሰድ የተሸለ ስራ ለመስራት ጥረት እያደረጉ ይገኛሉ።

ከመንግስት አስፈጻሚ አካላትም ጋር በመነጋገር ዘመናዊ አሰራሮችንና ቴክኖሎጂዎችን ለመተዋወቅ ጥረት እያደረጉ እንደሆነ የምትገልጸው ሳሮን በሌላ በኩል በዘርፉ ዘመናዊ የተባሉ ማሽኖች በመጠቀም የምርት ጥራትና በብዛት ማምረት ላይ ትኩረት ሰጥተው እየሰሩ እንደሚገኙ ታዝበናል።

ሳሮን በአሁኑ ሰዓት ከ280 በላይ የሚሆኑ ማሽኖችን ወደስራ ያስገባች ሲሆን ይህም በብዛትና በአጭር ግዜ ለማምረት ያስችላቸዋል።

የምርት ስታንዳርድ እንዳስቀመጡ የምትገልጸው ሳሮን የህጻናት ጂንስ በቀን 5ሺህ ያህል ማምረት እንደሚችሉና ለኤክስፖርት ስታንዳርድ የሚሆኑ ሸሚዞች በቀን እስከ 6 ሺህ ድረስ ማምረት እንደቻሉ ትገልጻለች። ምርቶችቻውን በብዛት ማምረት ስለሚችሉ ከሞጆ በተጨማሪ መርካቶ ለሚገኙ አከፋፋዮች በዝቅተኛ ዋጋ በብዛት እያቀረቡ ይገኛሉ።

በተጨማሪም የተለያዩ ጨረታዎችን በመሳተፍ በሚጠየቁበት ከተሞች ያደርሳሉ።

ለገበያ የሚሆኑ ሸሚዞችንና ቲሸርቶችን በብዛት ማምረትና የማቅረብ ስራዎች ጀምረናል የምትለው ሳሮን ለበዓላት የሚሆኑ ልብሶችን በተለይም የህጻናት ልብሶችን በስፋትና በጥራት የማምረት ስራ እንደሚሰሩና ጥራቱን የጠበቁ ምርቶችን ለማምረት የተሻሉና እሴት የሚጨምሩ ማሽነሪዎችን ከውጭ በማስመጣት በጥራትና በብዛት በማምረት ገበያው ላይ ተመራጭ ለመሆን እንሰራለን ትላለች።

በቀጣይም በሞጆ፣ ቢሾፍቱ፣ አዳማና አዲስ አበባ ገበያ የራሳቸውን ምርቶች በብዛት ለማቅረብ እቅድ ይዘዋል።

አሁን ሀገራችን ባለው ወቅታዊ ሁኔታ ገበያው የመቀዛቀዝ ሁኔታ እንደሚታይ የምትገልጸው ሳሮን በዚህም ምክንያት ምርታቸውን በስፋት ወደገበያ ማቅረብ እንዳልቻሉ ትናገራለች።

ድሮ መጥተው ሲያሰሯቸው የነበሩ ደንበኞች ገበያው በመቀዝቀዙ ምክንያት መምጣታቸውን እያቆሙ በመሆኑ የገበያ ክፍተት እያጋጠማቸው እንደሆነ የምትገልጸው ሳሮን በተጨማሪ የጥሬ እቃ አቅርቦት በሚፈልጉት መጠን ለማግኘት እየተቸገሩ እንደሆነና ትናገራለች።

እነዚህ ተግዳሮቶች ቢኖሩም ስራ ላለማቋም የተለያዩ ጥረቶችን እያደረግንና ይህ ግዜ እንደሚያልፍ እምነቱ ስላለን ገበያ ለማግኘት የተለያዩ ስራዎችን እየሰሩ እንደሆነና ት/ቤቶችና ሆቴሎች ጋር በመሄድና የተለያዩ ብሮሸሮችና ማስታወቂያዎችን በመስጠት ደንበኞችን ለማብዛት እየሰሩና ችግሩን ለማሳለፍ እየሞከሩ መሆኑን ትገልጻለች።



ድርጀቱን ለማስተዋወቅ በየትኛውም ከተሞች ላይ በሚገኙ ኤግዚቢሽንና ባዘሮች በመገኘት የማስተዋወቅ ስራ እየሰራን ነው የምትለው ሳሮን በራሳችው ባዛሮችን በማዘጋጀት የማስተዋወቅ ስራ እንደሚሰሩና የተለያዩ ብሮሸሮች፣ ባነሮችንና ስቲከሮች በማሰራት ድርጅታቸውን የማስተዋወቅ ስራ እየሰሩ ይገኛሉ፡፡

በሌላ በኩል በሶሻል ሚዲያዎች አማካኝነት ምርቶቻቸውን በማስተዋወቅ፣ ከደንበኞቻቸው የሚያገኙትን አስተያየቶችን በመጠቀም ድርጅታቸውን የበለጠ ለማስተዋወቅ እየሰሩ እንደሆነ ትገልጻለች፡፡

እዚህ ለመድረስ የበቃሁት ተግቼ መስራት በመቻሌ ነው የምትለው ሳሮን ‹‹የቀረበልኝን የድጋፍ አጋጣሚዎች መጠቀም፤ የሌሎችን ደግሞ በራሴ መፍጠር በመቻሌ ለስኬት በቅቻለሁ›› ትላለች፡፡

‹‹ማንኳኳት ያሉብኝን በሮች ሁሉ አንኳኳ ነበር›› የምትለው ሳሮን ‹‹ደንበኞቼን በአግባቡ በማስተናግድ በብዛትና በጥራት ማምረት ላይ ትኩረት በመስጠቴ ውጤታማ መሆን ችያለሁ›› ትላለች፡፡

ለስራና ለቀጠሮ ታማኝ መሆን በዘርፉ ወሳኝ መሆኑን የምትገልጸው ሳሮን ቀንና ሌሊት መስራት ካለባቸው እየሰሩ እዚህ ደረጃ መድረሳቸውን ትገልጻለች፡፡

ወደዚህ ሴክተር መግባት ለሚፈልጉ ወጣቶች ስኬት ላይ ለመድረስና ውጤታማ ለመሆን መንገዶች አልጋ በአልጋ አይሆኑም የምትለው ወጣቷ አንዱ መንገድ ሲዘጋ ሌላውን በትግስት በመሞከርና ተስፋ ባለመቁረጥ መስራት ይጠይቃል ትላለች፡፡

የሚያጋጥሙ ውጣ ውረዶችን በብልሃትና በትግስት በማለፍ መስራት እንደሚጠይቅና ያሰቡት ጋር ለመድረስ ብዙ መሰናክሎችና ተስፋ የሚስቆርጡ ነገሮች ቢያጋጥሙም ጠንክሮ በመስራት መድረስ እንደሚቻል ትናገራለች፡፡

በሌላ በኩል የመንግስት አስፈጻሚ አካላት ለዘርፉ ትኩረት በመስጠት በየደረጃው በተለይም ኢንተርፕራይዞች በሚቋቋሙበትና ስራ በሚጀምሩበት ወቅት ያሉ ግዚያት ፈታኝ በመሆናቸው ድጋፋቸውን አጠናክረው እንዲቀጥሉና ድጋፎችን በየደረጃው በመስጠት ዘርፉን ለማሳደግ በርትተው እንዲሰሩ ጥሪ ታቀርባለች፡፡

ወጣቷ እዚህ ደረጃ ለመድረስ ብርታት ለሆናት ፈጣሪ ምስጋናዋ የላቀ መሆኑን፣ አጠገቧ ለነበሩት ቤተሰቧቿ ትልቅ አክብሮትና ምስጋና እንዳላት፣ ለኢትዮጲያ ኢንተርፕራይዝ ልማት አመራሮችና ሰራተኞች፤ ሞጆ ከተማ ለሚገኙ መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ አካላት ላደረጉላት ድጋፍ የላቀ ምስጋናዋን አቅርባለች፡፡



# ካሜራችን


HASCO
HAND SANITIZER
500 ml
250 ml
Antiseptic
DISINFECTANT
DISINFECTANT

የኢትዮጵያ
ኢንተርፕራይዝ ልማት

## የማህበራዊ ሚዲያ አድራሻዎቻችን

**Facebook:** www.facebook.com/ethiopianenterprisedevelopment
**Telegram:** https://t.me/ethiopianenterprisedevelopment
**Website:** www.sme.gov.et
**Email:** ethiopianenterprise@gmail.com
**Youtube:** Ethiopian Enterprise Development
**Tell:** +251-11-551-11-22

ኢትዮጵያዊ አምራችነት፤ ከልምምድ ወደልማድ!